የፍርድ ቤቶች የወንጀል ስልጣን
እና
ክስ ስለ መስማት

ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች
የተዘጋጀ ፅሑፍ

አዘጋጅና አቅራቢ
ኃይለማርያም ሞገስ
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት
ዳኛ

መጋቢት ወር 2007 ዓ/ም

የስልጠናው ዓላማ

ስልጣኞች በቅርቡ ከወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ለፍተኛ ፍርድ ቤት የተሾሙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚጠይቀው ሃላፊነት እና ችሎታ ግምት ውስጥ በማስገባት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ህግ በማስፈፅም ረገድ የሚታዩ ዋናዋና ክፍተቶች በተመከተ በመጠኑም ቢሆን ለማስጨበጥ ነው፡፡በተለይም የወንጀል ስነ ስርዓት ሕግ ከሕገ መንግስት ጋር ስላለው ግንኙነት፣ስለ ፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይ ስልጣን፣የፍርድ ቤቶች የወንጀል ስረ ነገር እና የግዛት ክልል ስልጣን፣ስለ ክስ መስማትና ማስረጃ አቀራረብ እንዲሁም ስለ ክስ መስማትና የሙግት ሂደት በተመለከተ ያሉትን አንኳር ክፍተቶች ለማስገንዘብ ነው፡፡

መግቢያ

በዚህ ርዕስ የፍርድ ቤቶች ስልጣን እና የክስ መሰማት ሂደትን የምንመለከት ሲሆን በቅድሚያ የምንመለከተው ፍርድ ቤቶች ወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ያላቸው ስልጣን ይሆናል፡፡የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ በወጣበት ወቅት የነበረው አሃዳዊ የመንግስት ስርዓት አሁን ካለው የፌዴራል ስርዓት በእጅጉ የተለየ በመሆኑ በዚያው ልክ ፍርድ ቤቶችም የፌዴራል እና የክልል ተብለው የተከፈሉ በመሆኑ በፊት ከነበረው የፍርድ ቤቶች ስልጣን ለውጥ ተደርጓል፡፡በእርግጥ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የፌዴራል እና የክልል ጉዳዮች ተብለው የተመለከቱ ቢሆንም ህጉ ጥቅል ከመሆኑ የተነሳ ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡ህገ መንግስቱን ተከትለው በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጡት አዋጅ ቁጥር 25/88 እና ይህንኑ ባሻሻለው አዋጅ ቁጥረ 321/95 ድንጋጌዎች የክልል እና የፌዴራል ጉዳዮችን ተብለው የተለዩ ቢሆንም በእነዚህ ህጎች ያልተካተቱ ወንጀሎችን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መፍትሄ የሚሰጡ ባለመሆኑ ዳኞች ሲደናገሩ ይታያል፡፡ስለሆነም እነዚህ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ህጎች እና መደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በስረ ነገር ስልጣን ረገድ ያስቀመጧቸው መርሆች ለመዳሰስ ይሞከራል፡፡

ከዚህም ባሻገር በክስ መስማት ሂደት አዘውትረው የሚነሱ ክርክሮችን በማንሳት ውይይት ይደረግባቸዋል፡፡አብዛኞቹ ክርክሮች ከግንዛቤ እጥረት ይከሰታሉ ተብሎ የሚገመት በመሆኑ ከዚህ ስልጠና በመጠኑም ቢሆን ግንዛቤ በመውሰድ ህጎቹን በማስፈፀም ረገድ የተሻለ ውጤት ይገኛል የሚል እምነት አለን፡፡

I. የፍርድ ቤቶች ስልጣን

1.1 አጠቃላይ

- ፍርድ ቤቶች አንድ ክስ ከቀረበላቸው በኋላ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ማየትና ማራጋገጥ ያለባቸው ጉዳዩ ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑ አለመሆኑን ነዉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊመረምሯቸው የሚገባቸው ነጥቦች፤

- በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም (Judicial Jurisdiction)?
- የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በክልል ፍርድ ቤቶች ወይም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወይም ደግሞ ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ ባሉት አንደ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች፣ የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት እንዲሁም የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚታይ መሆኑ ወይም አለመሆኑ መለየት ተገቢ ነው።
- ጉዳዩ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ፍርድ ቤቶች በአንዱ የሚታይ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በየትኛው የፍርድ ቤት እርከን ሊታይ ይችላል የሚለውን የምንለይበት ሂደት ይከተላል።ይህ (Material Jurisdiction) የምንለው ነው።ከዚህ ጋር ተያይዞ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳይን በውክልና የሚያዩበት ስርዓት ስላለ ጉዳዩ የፌዴራልም ቢሆን በየትኛው የፌዴራል ፍርድ ቤት እርከን እንደሚታይ መለየት አስፈላጊ ነው። **(የክልል የከፍተኛ ፍርድ ቤት- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልል ጠ/ፍ/ቤት -የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን በውክልና እንደሚያዩ ይታወቃል። የፌ/ህገ መንግስት አንቀፅ** 80(2) እና(4)
- በየትኛው የፍርድ ቤት እርከን ጉዳዩ እንደሚታይ ከተለየ በኋላ **የት አካባቢ ባለ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ሊታይ ይገባል** የሚለውን ይለያል።ይህ ደግሞ **አካባቢያዊ ስልጣን** (Local Jurisdiction) ለምሳሌ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ በክልላችን ካሉት አስራ አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በየትኛው ፍርድ ቤት ይታያል የሚለውን የምንለይበት ነው።

- ስለሆነም በአጠቃላይ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በአራት ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነዉ።

1. የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያለቸው ስልጣን(Judicial Jurisdiction)
2. የክልል ወይም የፌዴራል ጉዳይ የማየት ስልጣን
3. በወንጀሉ ዓይነት በሚደረገው ክፍፍል መሰረት ያላቸው ስልጣን ናቸው(marerial Jurisdiction)
4. በተለያየ ቦታ የሚገኙ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያላቸው ስልጣን(Local Jurisdiction) ናቸው።

1.2. የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች አንድን የወንጀል ጉዳይ ለማየት ያላቸው ስልጣን (Judicial Jurisdiction)

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ፍርድ ቤቶች አንድ የወንጀል ጉዳይ ሲቀርብላቸው በቅድሚያ ሊያረጋግጡ የሚገባቸው ጉዳዩ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ሊያይ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ነው።ይህ ማለት ግን ፍርድ ቤቶቹ አንድ ጉዳይ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ይታያል ወይስ አይታይም የሚለው ጥያቄ የሚያነሱት በሁሉም ጉዳዮች ላይ አይደለም። ይልቁንም ይህንን ጥያቄ የሚያነሱት ከወጭ አገር ጋር ንክኪ(Foreign element) ያለው እንደሆነ ነው። foreign element የምንለው የወንጀል ፈፃሚው ዜግነት፤ የተፈጸመበት አገር፤ ወንጀሉ አለም አቀፋዊ መሆን የመሳሰሉት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

1.2.1. በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስለሚዳኙ ሰዎች

አንድ ሰው በኤፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመወሰን፡-

ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ፣

ለ) የተከሳሹ ዜግነት፣ እና

ሐ) የተፈፀመው ወንጀል ዓይነት መሰረት በማድረግ እንደሆነ ከህጉ አጠቃላይ መንፈስ መገንዘብ ይቻላል።የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች አንድን ወንጀል ለማየት ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን የሚገዙ ድንጋጌዎች የሚገኙት በፍሬ ነገር ህጉ ማለትም በኢትዮጵያ ወ/ህግ እንጅ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ አይደለም።ስለሆነም በወ/ህጉ ከአንቀፅ 11 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች መመልከት አስፈላጊ ነው።የእነዚህ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ስንመለከት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች አንድን ወንጀል ለማየት ያላቸው ስልጣን በሁለት ይከፈላል።እነዚህም፡- ዋና ስልጣን (Principal Jurisdication) ወይም ምትክ (Subsidiary Jurisdication) ተብለው ይጠቀሳሉ።

የዋና ስልጣን እና ምትክ ስልጣን እንዲሁም በመካከላቸው ያለው ልዩነት ከዚህ በታች በአጭሩ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

1) ዋና ስልጣን (Principal Jurisdiction) እና የዋናው ስልጣን ወሰን (የወንጀል ሕግ ቁጥር ከ11-16)

ዋና ስልጣን

የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በአንድ የወንጀል ጉዳይ ላይ ዋና ስልጣን አላቸው ማለት ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ አገር ይሁን በኢትዮጵያ፤ፈፃሚው ኢትዮጵያዊ ይሁን የውጭ ዜጋ እንዲሁም ጉዳዩ በውጭ አገር ይታይ አይታይ ግምት ውስጥ ሳይገባ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ያላቸውን ስልጣን የሚያመለክት ነው፡፡ስለሆነም የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በሚከተሉት ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡

1) ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል **የፈፀመ ማንኛውም ሰው**፡፡
2) በውጭ አገር ሆኖ **በኢትዮጵያ ላይ ወንጀል ፈፅሟል** ተብሎ የተከሰሰ ማንኛውም ሰው ፣
3) በውጭ አገር የማይደፈር መብት (Immunity) ያለው የኢትዮጵያ መንግስት ሰራተኛ በውጭ አገር ወንጀል ሰርቷል ተብሎ የተከሰሰ ሰው፤ እንዲሁም
4) በውጭ አገር ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ የኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት አባል የሆነ ሰው ናቸው፡፡

በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ወንጀል ቢፈፀም የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ዋና ስልጣን ያላቸው ሲሆን የኢትዮጵያ የወንጀል ህግም ተፈጻሚ ይሆንባቸዋል፡፡ይህንኑ ሁኔታ በዝርዝር እንመልከታቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚሰሩ ወንጀሎች (ከቁጥር 11-12 ይመለከታል)

በወ/ህ/ቁ.11 (1) በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በወንጀል ሕግ ከተጠቀሱት ማንኛውንም ወንጀል የሰራ ማነኛውም ሰው በዚሁ ሕግ መሰረት እንደሚቀጣ ይገልፃል::(**ግዛት ሲባል የብስና አየርም ይጨምራል**)፡፡

በአለም አቀፍ ህግ መሰረት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ ውስጥ ወንጀል የፈጸመ ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ መሰረት ይዳኛል፡፡

ለምሳሌ:- አንድ የቻይና ዜጋ የሆነ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት የወ/ህ/ቁ.555(ለ) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ከባድ የአካል ጉዳት ወንጀል ቢፈፅም ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በመሆኑ ተከሳሹ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር ነው::

ለምሳሌ:- አንድ የደቡብ ሱዳን አየር መንገድ አውሮፕላን በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ሲበርር አውሮፕላኑ ውስጥ አንዱ የኬንያ ዜጋ ሌላውን የኬንያ ዜጋ ቢደበድበው ወንጀሉ የተፈፀመው ኢትዮጵያ አየር ላይ በመሆኑ (አየሩ የኢትዮጵያ ግዛት ነው) ወንጀሉ የተሰራው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ነው::ይህም ደብዳቢውን በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስር ያደርገዋል::ስለዚህም በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ተላልፈሃል ተብሎ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል::

- በዓንቀፅ 11(3) እንደተመለከተው አንድ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል ሰርቶ ከኢትዮጵያ አምልጦ በሌላ አገር ጥገኝነት ጠይቆ ቢቀመጥ የኢትዮጵያ መንግስት ወንጀለኛውን በጥገኝነት ያስቀመጠው መንግስት አሳልፎ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል::የኢትዮጵያ መንግስት ይህ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግን የዚህ ዓይነት ስምምነት(Reciprocity) ጥገኝነትን ከሰጠች አገር ጋር ያለው እንደሆነ ነው:: ስምምነት ከሌለ ጥገኝነት በሰጠች አገር እንዲከሰስና እንዲፈረድበት ኢትዮጵያ መጠየቅ ትችላለች::
- የኢትዮጵያ መንግስት በጠየቀው መሰረት በዛው አገር ተከስሶ ነፃ የተባለ እንደሆነ ወይም በውጭ አገር ተፈርዶበት ምሕረት ወይም ይቅርታ ተደርጎለት እንደሆነ ወይም ክሱ ወይም ቅጣቱ በይርጋ ምክንያት ተሰርዞለት እንደሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ቢያዝም ሊከሰስና ሊቀጣ አይቻልም (ዓንቀፅ 12(2)::
- ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት ተጠርጣሪው ጥገኝነት በጠየቀበት አገር ውስጥ እንዲከሰስ አስጠጊውን አገር ባይጠይቅና አስጠጊው መንግስት ራሱ ከሰሶ በነፃ ቢለቀውና በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ እንደገና በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል:: (**ዓንቀፅ** 16(2))::
- ሌላው በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ ሳይፈፅም ወይም በከፊል ብቻ ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ ቢገባ **ያልተፈፀመው ቅጣት በኢትዮጵያ ይፈፀማል** (ዓንቀፅ 12(3)):: ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ግን በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ነው::

በውጭ አገር በኢትዮጵያ ግዛት ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች (ዓንቀፅ 13)

ይህ ዓንቀፅ የሚመለከተው **በኢትዮጵያ መንግስት በደህንነቱ** ወይም **አንድነቱ ላይ** ወይም **በሕጋዊ ተቋማቱ** ወይም **ዋና ዋና ጥቅሞቹ** ወይም **በግንዘቡ ላይ** ወንጀል በፈጸመ በማናቸውም ሰው ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ነው:: አነዚህ ወንጀሎች በወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 238 - 260 እና 355 - 374 ስር የሚወድቁ ናቸው::

<u>ለምሳሌ</u>:- አንድ የውጭ አገር ዜጋ በውጭ አገር ሁኖ የሐሰት ግንዘብ (በኢትዮጵያ ግንዘብ መልክ) ቢያሳትም በዓንቀፅ 238 እና 357 የተደነገጉትን የጣሰ በመሆኑ በዓንቀፅ 13 መሰረት **በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ነው::**

የማይደፈር መብት ያለው የኢትዮጵያ የመንግስት ሰራተኛ እና የኢትዮጵያ መንግስት የመከለከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር ሆኖው የሚፈፅሟቸው ወንጀሎች፡፡ (ዓንቀፅ 14 እና 15)፡

- በውጭ አገር ያሉ የማይደፈር መብት ያላቸው የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣኖች ሁሉ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ናቸው:: በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት መከላከያ ሰራዊት አባላትም እንደዚሁ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሲሆኑ ነገር ግን እንደ ወንጀሉ ዓይነት አንዳንድ ጊዜ በዋና ስልጣን ሌላ ጊዜ ደግሞ በምትክ (አነስተኛ) ስልጣን ስር የሚወድቁበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል::

- ሌሎች በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ ተራ ዜጎችም **በወ/ህ/ቁ.13** ስር የተመለከተው ወንጀል (**በኢትዮጵያ መንግስት በደህንነቱ** ወይም **አንድነቱ ላይ** ወይም **በሕጋዊ ተቋማቱ** ወይም **ዋና ዋና ጥቅሞቹ** ወይም **በግንዘቡ ላይ** የሚፈፀም ወንጀል) ከፈፀሙ በዋና ስልጣን ስር ይወድቃሉ፡፡ከዚህ ውጭ ያሉት ወንጀሎች ቢፈጽሙ ግን በምትክ ስልጣን ስር ይወድቃሉ ማለት ነው፡፡

- የማይደፈር መብት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን በውጭ አገር በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሊወድቁ የሚችሉ (በዓንቀፅ 13 ከተመለከተው ውጭ) በኢትዮጵያ እና **ወንጀል በተፈፀመበት አገር ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ነው::**

- የመከላከያ ሰራዊት አባል በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ከዓንቀፅ 269 **እስከ** 322 የተጠቀሱትን ወንጀሎች በመስራት የዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም ወታደራዊ

ጠባይ ያለውን ወንጀል የሰራ እንደሆ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሆኖ በሦር ፍርድ ቤት ላይ ይከሰላል:: ከዓንቀፅ 269 እስከ 322 ውጭ የሆኑትን ድንጋጌዎች ቢጥስ ግን በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው የሚሆነው::

የዋናው ስልጣን ወሰን (የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 16)

(1) በዋናው ስልጣን ላይ ያለው ወሰን ወንጀለኛው በውጭ አገር ተፈርዶበት የተቀጣው ቅጣት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚወሰንበት ቅጣት ላይ የሚቀነስበት መሆኑ ብቻ ነው::ይህ ማለት የኢትዮጵያ መንግስት ሳይጠይቅ በውጭ አገር ተከሶ ቅጣት ተወስኖበት ተወሰነ ቅጣት ፈጽሞ በኢትዮጵያ በድጋሚ ተከሶ ቅጣት ቢወሰንበት በውጭ የፈጸመው ቅጣት ይቀነስለታል::ይህ ዋና ስልጠን ወሰን ተብሎ ይጠቀሳል::

(2) ሆኖም ወንጀሉን የፈፀመው ሰው በውጭ አገር ፍርድ ቤት ተከሶ የተፈረደበት በኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ መሰረት ከሆነ (የወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 12) ወንጀለኛው በኢትዮጵያ ዋና ድጋሚ አይከሰስም::

(3) የማይደፍር መብት ባላቸው ኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ መልእክተኞች በዋና ስልጣን ስር ቢሆኑም ወንጀሉ በኢትዮጵያ እና በዚያው አገር ህግ ወንጀል ተደርጎ ካልተደነገገ አይከሰሱም:: በአንቀፅ 13 የተጠቀሰው ወንጀል ግን በዚያው አገር ወንጀል ባይሆንም ይቀጣሉ:: እንዲሁም ወንጀሉ በኢትዮጵያና በዚያ አገር በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስከስስ ከሆነ እና አቤቱታ ካልቀረበ ሊከሰሱ አይችሉም::

2) ምትክ / አነስተኛ/ ስልጣን (Subsidiary Jurisdiction)

የአነስተኛ ስልጣን ፍቺው ተሰራ የተባለው ወንጀል ኢትዮጵያን በጣም የማይነካ ወይም የማይጎዳ ሲሆን ነው::የሚከተሉትን ወንጀሎች የፈፀሙ ተከሳሾች በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ናቸው::

ሀ) በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥስ ወይም የህዝብን ጤንነትና ሞራል የሚጎዳ ወንጀል ሰርተዋል በመባል የተከሰሱ ግለሰቦች፣

ለ) በውጭ አገር አንዳንድ ወንጀሎችን በኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ፈፅመዋል በመባል የተከሰሱ እና

ሐ) በውጭ አገር በማንኛውም ሰው ላይ ከባድ ወንጀል ፈፅመዋል በመባል የተከሰሱ ኢትዮጵያዊያንና በውጭ አገር የአገሩን ተራ ሕግ በመጣስ ወንጀል ሰርተው አምልጠው ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ወታደሮች ናቸው፡፡

- **በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ስላሉ ሰዎች፣**

1. <u>በዓለም አቀፍ ሕግና ሰርዓት ላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ወንጀሎች (ዓንቀፅ 17)</u>

በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው ተብሎ የተደነገገውን ወንጀል የፈፀመ ወይም ኢትዮጵያ በተስማማችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት ወንጀል ነው ተብሎ የተወሰነውን የፈፀመ ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው:: ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ከዓንቀፅ 269 እስከ 283 የተዘረዘሩትን ሲሆኑ ፣ ሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱት ወንጀሎች ደግሞ በነጋሪት ጋዜጣና ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ወንጀል ጠቀስ በሆኑ ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ ናቸው::

በተጨማሪም የህዝብን ጤንነት ወይም ሞራል የሚነዱ ወንጀሎችን በውጭ አገር የፈፀሙ ሰዎች በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ናቸው:: እነዚህም ወንጀሎች በዓንቀፅ 525 (መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሓኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም)፤ በዓንቀፅ 599 እና 636 እስከ 641 የተመለከቱትን ናቸው::

2. *<u>ከኢ/ዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ሌሎች ወንጀሎች (ዓንቀፅ 18</u>)*

ሀ) በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር የሚሆነው፣ ያደረገው ጥፋት በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወይም ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከኢትዮጵያ ውጭ ከላይ በተመለከቱት (ዓንቀፅ 11-17) ከተገለፁት ወንጀሎች ሌላ የፈፀመ እንደሆነ፣ አድራጊው በዚሁ ወንጀል በውጭ አገር ሳይከሰስ ከቀረ ይህ የወንጀል ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል:: ይህ ለማድረግ ግን:-

(1) ድርጊቱ በተፈፀመበት አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጎ እንደሆነ፣ እና

(2) የተፈፀመው ወንጀል ከባድ በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ተከሳሹ ተይዞ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማድረግ በቂ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው::

ለምሳሌ:-አንድ ኬንያዊ በቻድ አገር አንድ ኢትጵያዊ ቢገድል እና ከቻድ አገር ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ከሌለ በቻድ አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ (ዓንቀፅ 540) ወንጀል ስለሆነ ገዳዩ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ይሆናል:: ምክንያቱም፤

1) ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ በመሆኑ ፣
2) ወንጀሉ በኢትዮጵያም በ "ሀ" ም አገር ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ በመሆኑ ፣ እና
3) ወንጀሉ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት አሳልፎ ለመስጠት በቂ ከባድነት ያለው በመሆኑ ነው::

ለ) ማንም የውጭ አገር ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ ሌላ ወንጀል ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ በገባ ጊዜ በዚህ ሕግ ተላልፎ ካልተሰጠ ወይም በሌላ አኳኃን ካልተደነገገ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰስ የሚችለው (በኢትዮጵያ አነስተኛ ስልጣን ስር የሚሆነው) የሰራው ወንጀል **ከአስር ዓመት ባለነሰ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ነው፡፡** (ዓንቀፅ 18(2)) በዚህ ጊዜ ወንጀሉ የተፈጸመው በኢትዮጵያዊ ላይ አይደለም፡፡

3. ***ከኢትዮጵያ ውጭ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል ስለሚሰራው ወንጀል (ዓንቀፅ 15(1)::***

ማንም የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር መደበኛ ሕግን ቢጥስ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ይሆናል:: ወንጀል በፈፀመበት አገር ሊከሰስና ሊፈረድበት ይቻላል:: ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ እንደሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ይዳኛል (ዓንቀፅ 21(2))::

የምትክ ስልጣን ወሰን (ዓንቀፅ 19(4) እና 20)

(1) በዓንቀፅ 19(4) እንደተመለከተው አንድ ሰው በውጭ አገር ወንጀል ሰርቶ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ቢሆን የውጭ አገሩና የኢትዮጵያ የወንጀል ሕጎች በሚደነግጉት ቅጣት መካከል ልዩነት ያለ እነደሆነ ተፈፃሚ የሚሆነው **ተከሳሹን የሚጠቅመው መሰረት በማድረግ ይሆናል::**

ለምሳሌ:- ወንጀሉ በተሰራበት አገር በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ በኢትዮጵያ ሕግ ግን በሞት የሚያስቀጣ ቢሆን የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተፈፃሚ የሚያደርጉት የዕድሜ ልክ እስራትን የሚያዘው ሕግ ይሆናል ማለት ነው::

(2) **አንድ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር የሚወድቅ ሰው በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ ከወጣ ወይም አያስከስሰውም ከተባለ እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማይከሰስ ከሕጉ መገንዘብ ይቻላል** (ዓንቀፅ 20(1))::

የዋና እና የምትክ ስልጣን ማጠቃለያ

ዋና ስልጣን

ሀ) የሚከተሉት ሰዎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዋና ስልጣን ስር ናቸው፡፡

1. በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወንጀል የሰሩ ሰዎች (ዓንቀፅ-11)
2. በውጭ አገር ከዓንቀፅ 238-260 እና 355-374 የተጠቀሱትን ወንጀሎች በኢትዮጵያ ላይ የሰሩ ሰዎች (ዓንቀፅ 13)
3. በውጭ አገር በአገሩ ሕግና በኢትዮጵያ ሕግ የተከለከለ ወንጀል የሰሩ በውጭ አገር የማይደፈር መብት ያላቸው የኢትዮጵያ መልእክተኞች (ዓንቀፅ 14)
4. ዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ ወይም በዓንቀፅ 269-322 የተመለከቱትን ወታደራዊ ሕግ በመጣስ በውጭ ኣገር ወንጀል የሰሩ የመከላከያ ሰራዊት አባላት (ዓንቀፅ 15)

ለ) የሚከተሉት ዋናውን ስልጣን የሚመለከቱ መሰረተ ሓሳቦች ናቸው፡፡

1. አንድ ወንጀለኛ በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ መውጣቱ አጥፊው የተከሰሰው በዓንቀፅ 12 መሰረት የኢትዮጵያ መንግስት ጥያቄ ኣቅርቦ ካልሆነ በስተቀር ወንጀለኛውን እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ ከመከሰስ አያድነውም (ዓንቀፅ 16(1) (2))
2. ወንጀሉን በሰራበት አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ በከፊል ወይም በሙሉ የተፈፀመበት ተከሳሽ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈረደበት ቅጣት ላይ በውጭ አገር የተፈፀመበት ቅጣት ይቀነስለታል (ዓንቀፅ 16(3))(ወሰን)

ምትክ ስልጣን

ሀ) የሚከተሉት ሰዎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር ናቸው፡፡

1. በውጭ አገር የአገሩን ተራ ሕግ በመጣስ ወንጀል ሰርተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት (ዓንቀፅ 15(1))
2. በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን በመጣስ (ዓንቀፅ 269 እስከ 286) ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ወይም ስምምነት ዓለም ዓቀፍ ወንጀል የተባሉትን በመጣስ ወይም በዓንቀፅ 525፣599፣637፣640 እና 641 በመጣስ ወንጀል የሰራ ማንኛውም ሰው (ዓንቀፅ 17) የውጭ አገር ዜጋም ይሁን ኢትዮጵያዊ)
3. በውጭ አገር በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወንጀል የሰራ ማነኛውም ዜጋ ወይም በውጭ አገር ወንጀል የሰራ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር የማይሆን ኢትዮጵያዊ፤ይኸውም የሚሆነው (1ኛ) ጥፋቱ በኢትዮጵያም በውጭው አገር ሕግም ወንጀል ሆኖ

ሲቆጠርና (2ኛ) ወንጀሉ በኢትዮጵያ ሕግ ወንጀለኛውን ኣሳልፎ የማይሰጥ ሲሆን ነው (ዓንቀፅ 18(2))

ለ) የሚከተሉት አነስተኛ ስልጣንን የሚመለከቱ መሰረተ ሓሳቦች ናቸው፡፡

1. በኢትዮጵያ ውስጥ በአጥፊው ላይ የሚፈረደው ቅጣት ወንጀሉ በፈፀመበት አገር ሕግ ለወንጀሉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት አይበልጥም (ዓንቀፅ 19(4))
2. ወንጀለኛው በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ የወጣ ወይም ከክሱ የተሰናበተ እንደሆነ እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ ኣይከሰስም (ዓንቀፅ 20(1))
3. በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱ በከፊል የተፈፀመበት ወንጀለኛ ቅጣቱ በይርጋ ካልታገደ በስተቀር ቀሪው ቅጣት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲፈፀምበት ሊፈረድበት ይችላል (ዓንቀፅ 20(2))

1.3 በክልል፣ በፌዴራል እንዲሁም በሌሎች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ ባሉት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ወንጀሎች

1.3.1 የክልል ወይም የፌዴራል ጉዳዮች

- የኢፌዴሪ ሕገመንግስት የዳኝነት አካል በፌዴራልና በክልል ደረጃ እንደሚዋቀሩና የየራሳቸው የዳኝንት ስልጣን እንዳላቸው ይገልፃል፡፡ቁጥር 79(1)
- የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን በየክልሉ ብቻ የተወሰነ ሲሆን የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ግን በአ/አበባና ድሬዳዋ እንዲሁም እንደጉዳዩ ዓይነት ወደ ሁሉም ክልሎች ሊደርስ ይችላል፡፡
- በእርግጥ የወንጀል ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት መሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 55(2)(5) ስር የተመለከተ ቢሆንም ህጉን መሰረት አድርጎ ዳኝነት በመስጠት ረገድ ግን ክልሎች ስልጣን ያላቸው መሆኑ አዋጅ ቁጥር 25/88 እና ይህንኑ አዋጅ ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 321/95 ከወጡበት አላማ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

- በመሆኑም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 በዓንቀፅ 4 ላይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች እንዲታዩ ከተደረጉት ወንጀሎች ውጭ ያሉት ወንጀሎች በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ናችው፡፡ይህ የሚያሳየው የወንጀል ህጉ በፌዴራል መንግስት ቢወጣም በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ ህግ አውጭው (የኢፌዴሪ የህዝብ ተወ/ም/ቤት)ሃሳብ መሆኑ ነው፡፡

- ይሁን እና በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆኖው በክልሎች ውስጥ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች የክልል ፍ/ቤቶች በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 78 (2) ባገኙት ውክልና መሰረት ከራሳቸው ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሆነውን የወንጀል ጉዳይም ደርበው ያየሉ፡፡

(ሀ) የፌዴራል ጉዳዮች ከአዋጅ ቁጥር 25/88 እና ይህን አዋጅ ካሻሻለው አዋጅ ቁጥር 321/95 አንፃር ሲቃኝ

የፌዴራል ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳዮች ላይ ያላቸው ስልጣን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡-

1. በመንግስት ግዛት ሀገር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች(በአዋጅ ቁጥር 321/95) የተሻሻለ ከወ/ሕግ ዓንቀፅ 238-260)፣
2. በውጭ አገር መንግስት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 261-268) ፣
3. በሰው ልጆች መብት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች(Offences against the law of Nations) (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 269-283) ፣

   ከወ/ሀ/ቁ.598 ስር ያለው ክርክር ቢነሳ መልካም ነው፡፡
4. በፌዴራል መንግስቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
5. የሐሰት ገንዘብን በሚመለከቱ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 356-362) ፣
6. በፌዴራል መንግስት ሰነዶች ላይ የሐሰት ስራ በመስራት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
7. ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አግልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነፃነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
8. የበረራ ደህንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች ፣
9. (ሀ) ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቲክ ህጎችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሁነው ልዩ መብትና ጥበቃ(Immunity) ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች ፣

   (ለ) ከአምስት ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ የውጭ አገር ዜጎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፡(በአዋጅ ቁጥር 321/95) የተሻሻለ)

- በ(ሀ) እና በ(ለ) ክፍል የተጠቀሱት ጽንሰ ሃሳቦች ተመሳሳይ ይመስላሉ እንጂ በማካከላቸው ሰፊ ልዩነት አለ በ(ሀ) ላይ የተጠቀሰው በውጭ አገር መንግስታት ወይም በአለም አቀፍ ድርጅቶች የተላኩ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ልዩ ጥበቃ ያላቸው ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ተበዳይ ወይም ከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች የፌዴራል ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ማለት ወንጀሉ ከባድ ይሁን ቀላል ወይም የቅጣቱ መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ መሆኑ ነው፡፡
- በ(ለ) ክፍል የተጠቀሰው ኮንሴፕት ደግሞ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ግለሰቦች ውጭ የሆኑ ተራ የውጭ አገር ሰዎች የግል ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች ሁነው ነገር ግን ወንጀሎቹ ከአምስት ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ሲሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ይሆናል ማለት ነው፡፡ወንጀሎቹ ከአምስት ዓመት እና ከዚያ በታች የሚያሰቀጡ ከሆኑ ግን ጉዳዩ በክልል ፍርድ ቤቶች ሊታዩ የሚችል መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡1 አንድ የከናዳ ዜጋ ለጉብኝት በመጣበት ወቅት ተራ የውንብድና ወንጀል ቢፈጸምበት ጉዳዩ የፌዴራል ይሆናል፡፡ምክንያቱም ወንጀሉ ከአምስት ዓመት በላይ ስለሚያስቀጣ ፡፡ነገር ግን ይህ ግለሰብ ቀላል ስርቆት ወንጀል ቢፈጽም ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ከዚህ ልንገነዘብ የሚገባን ቁም ነገር ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ አገር ዜጋ መሆኑ ወይም የግል ተበዳዩ የውጭ አገር ዜጋ መሆኑ ብቻ ጉዳዩ የፌዴራል አያደርገውም፤፤ፌዴራል ወይም ክልል ብሎ ለመወሰን ወንጀሉ ምንያህል እንደሚያስቀጣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

10. አደገኛ እና አደንዛዥ እፆች ህገወጥ ዝውውርን የሚመለከቱ የሚመለከቱ ወንጀሎች፣
11. በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌዴራልና በክልል ፍ/ቤቶች የስልጣን ክልል ስር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች ፣ እና
12. የፌዴራል መንግስቱ ባለስልጣኖችና ሰራተኞች በስራቸው ወይም በሃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ በሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፣
13. በተለያዩ ብሄሮች ብሄረሰቦች ጎሳዎች ኃይማኖቶች ተከታዮች ወይም የፖለቲካ ቡድኖች መካከል የተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤(በአዋጅ ቁጥር 321/95 የተጨመረ)
14. በፌዴራል መንግስት ንብረቶ ላይ የሚፈጸሙ እና ከአምስት ዓመት ጽኑ አስራት በላይ የሚያስቀጡ ወንጀሎች (በአዋጅ ቁጥር 321/95 የተጨመረ)

እዚህ ላይ በፌዴራል መንግስት ንብረቶች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ሁሉ የፌዴራል ጉዳይ አይሆንም፡፡ይልቁንም ጉዳዩ የፌዴራል ለመሆን ወንጀሉ ከአምስት ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል መሆን አለበት፡፡ከዚህ ውጭ ያሉት ወንጀሎች የክልል ጉዳዮች በመሆናቸው በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ናቸው፡፡

(ለ) በሌሎች ህጎች በግልጽ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ

ከዚህ ጋር ተያይዞ በአዋጅ ቁጥር 25/88 እና በማሻሻያው 321/95 በግልጽ ያልተሸፈነ ጉዳይ ሁኖ በአዋጅ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በግልፅ የተሰጡ ጉዳዮች አለ፡እነዚህም ለመጥቀስ ያህል

- **ኮፒ ራይት የሚመለከቱ ወንጀሎች**

በአዋጅ ቁጥር 410 አንቀጽ (2)(9) ስር በግልፅ እንደተመለከተው የቅጅ ወንጀሎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊታዩ የሚገባ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

- የፀረ ሽብር አዋጅ 652/2001 አንቀፅ 2(1) ...በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- የጸረ ሙስና አዋጅ ቁጥር 343/97 አንቀፅ 7.. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- አዋጅ ቁጥር 501/98 የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አንቀጽ49 ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች
- አዋጅ ቁጥር 780/2005 በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርን በገንዘብ መርዳት ...ለፌ/ል ለከፍ/ፍ/ቤት

ከዚህ ድንጋጌ ለመገንዘብ እንደሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 25/88 እና በማሻሻያው አዋጅ 321/95 በግልጽ ቢሸፈንም ባይሸፈንም በአንዳንድ አዋጆች በግልፅ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሊሰጥ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ይህ ማለት ግን ከፍ ብሎ የተጠቀሱት አዋጆች ብቻ ናቸው ማለት አይደለም፡፡እነዚህ አዋጆች ለማሳያ አነሳን እንጂ ሌሎች አዋጆች ሊኖሩ ስለሚችሉ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1.3.2 ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭ ባሉ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ወንጀሎች

(ሀ) ወታደራዊ ጉዳዮች (አዋጅ ቁጥር 27/88 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 343/1995)

አልፎ አልፎ ወታደራዊ ጉዳዮች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሲዳኙ ይታያሉ፡፡ይሁን እንጂ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸው የስረ ነገር ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 27/1988 አንቀጽ 26 ስር በግልፅ ተመልክቷል፡-

- ከወ/መ/ህ/ቁ.296 እስከ 331 ድረስ የተጠቀሱት ወንጀሎችን ፈፅመው ተጠያቂ የሚሆኑ ሰዎች፣
- በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር የሚፈጽመው ማንኛውም ወንጀል
- በውጭ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታደር ጋር አብረው የሚዘምቱ ሲቪሎች
- በጦር ምርኮኞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ናቸው፡፡

በንዑስ ቁጥር 1 ስር የተጠቀሰው ድንጋጌ ስንመለከት አንድ ጉዳይ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ስር እንዲወድቅ የሚወድቅ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ለመለየት በመስፈርት የተቀመጠው የወንጀሉ አይነት ነው፡፡ከወ/ህ/ቁ.296 እስከ ወ/ህ/ቁ.331 ስር የተጠቀሱት ወንጀሎች የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወታደራዊ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የሚታይ መሆኑ ነው፡፡ፈጻሚው የግድ ወታደር ሊሆን አይጠበቅም፡፡ስልጣኑ የሚመራው የተፈፀመው የወንጀል አይነት ነው፡፡

በንዑስ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ በውጭ አገር በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ካለ ወታደር ጋር አብረው የዘመቱ ሲቪሎች የሚፈጽሟቸው ማናቸውም ወንጀሎች በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታዩ መሆኑ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ ስልጣኑን የሚመራው በፈጻሚዎቹ ማንነት ነው፡፡

በንዑስ ቁጥር 4 ስር የተጠቀሰው በጦር ምርኮኞች ላይ የተፈጸመ ወንጀል በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታይ መሆኑ ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ስልጣኑ የሚመራው በግል ተበዳዩች ማንነት ነው፡፡

በንዑስ ቁጥር 2 ላይ በግልጽ የሚያሳየው በግዳጅ ላይ ያለ ወታደር የሚፈጽመው ወንጀል በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታይ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

ግዳጅ የሚለው በአዋጅ ቁጥር 27/1988 ላይ ትርጉም ያልተሰጠው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 343/95 **አንቀፅ** (2)(9) ስር ትርጉም ተሰጥቶታል፡የትርጉሙ ይዘት በሚከተለው ተገልጿል፡፡ግዳጅ ማለት “ **ማንኛውም የሰራዊት አባል ከተቀጠረበት ጊዜ አንስቶ ከሰራዊት እስከሚሰናበትበት ጊዜ ድረስ በመከላከያ ውስጥ የሚያከናውነው የውትድርና ተግባት ነው**” ይላል፡፡ከዚህ ህግ ትርጉም መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ሰው ወታደራዊ ድዳጅ ላይ ነው የሚባለው (1) የመከላከያ የሰራዊት አባል መሆን አለበት (ከቅጥር እስከ ስንብት) (2) የሚያከናውነው ስራ ውትድርና ተግባር መሆን አለበት፡፡

<u>ምሳሌ 1 ፤ አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል በጥበቃ ላይ እያለ ከአንድ ሲቪል ጋር ተጣልቶ በጥይት ቢገድለው ጉዳዩ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ይታያል ማለት ነው፡፡</u>

ምሳሌ 2 የመከላከያ ሹፌር ከአንድ እዝ ወደ ሌላ እዝ በመጓዝ ላይ እያለ በከተማ ውስጥ ውስጥ ሲጓዝ ሰው ገጭቶ ቢገድል ጉዳዩ በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታይ ይሆናል፡፡ምክንያቱም

ወንጀሉ የተፈጸመው በመከላከያ ካምፕ ባይሆንም የተፈጸመው በመከላከያ ሰራዊት አባል በመሆኑ እና የፈጸመውም በግዳጅ ላይ በመሆኑ ጉዳዩ በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታይ ይሆናል፡፡

ምሳሌ 3 ለእረፍት ወደ ቤተሰቦቹ የሄደ መከላከያ ሰራዊት አባል በዚያው በአካባቢው የስርቆት ወንጀል ቢፈፅም ወንጀሉ በፈጸመበት ጊዜ መከላከያ አባል ቢሆንም ወንጀሉ በፈጸመበት ጊዜ የውትድርና ተግባር ሲያከናውን ያልነበረ በመሆኑ በወታደራዊ ፍርድ ቤት ሊታይ አይገባም፡፡

ምሳሌ 4 አንድ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ገንዘብ ያዥ ሁኖ ሲሰራ የነበረ ወታደር አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የመከላከያ ሰራዊት ቢሮ ውስጥ ገንዘብ አጉድሎ ቢገኝ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚከሰሰው የት ነው?

- ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ሰ/ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.33368 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይመልከቱት፡፡

(ለ) ለከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የወንጀል ነክ ጉዳዮች

ከፍ ሲል በግልፅ እንደተመለከተው ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በግልፅ ያልተሰጡ ጉዳዮች በክልል ፍርድ ቤቶች ሊታዩ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡በክልል ፍርድ ቤቶች ሊታዩ ከተተው ጉዳዮች ውስጥ የክልላችን ምክር ቤት አዋጅ በማውጣት ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በክልላችን ውስጥ የሚገኙ ሶስት የከተማ ምክር ቤቶች(ጎንደር፣ደሴ እና ባህር ዳር) ደንብ በማውጣት የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የተወሰኑ የወንጀል ጉዳዮች እንዲያዩ ተደርጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 151/200 አንቀፅ 13 ስር በግልፅ ለማ/ፍ/ቤቶች ስልጣን የተሰጡትን ሳይጨምር በወንጀል ህግ 7ኛ እና 8ኛ መጽሃፍ ውስጥ የተመለቱት ከወ/ህ/ቁ.734 እስከ 865 ስር የተመለከቱት የደንብ መተላለፍ ወንጀሎት በከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ሊታዩ የሚችሉ እንደሆነ ተመልክቷል፡ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 10(2)(መ) ስር በግልፅ እንደተመለከተወው በወ/ህ/ቁ.33(ብርበራ)፣35(ቀዳሚ ምርመራ)፣53(መያዣ ትዕዛዝ)፣59(ጊዜ ቀጠሮ) እና 64(ዋስትና) መሰረት በሚነሱ ጉዳዮች አከራክረው ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑ ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ የደንቡ መሰረት በሆነው በእናት አዋጅ ቁጥር 91 /1996 አንቀፅ 57 ስር በግልፅ ያልተመለከቱ በወ/ህ/ቁ.33፣35፣53፣59 እና 64 ስር በተጠቀሱት ጉዳዮች ፍርድ ቤቶቹ እንዲያዩ በደንብ መሰጠቱ ደንቦቹ በእናት አዋጁ ያልተሰጠን ስልጣን ማካተታቸው ህጋዊ ስላልሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖራቸው አይገባም የሚል ክርክር የሚያነሱ ዳኞች እንዳሉ ሁሉ ደንቦቹ በከተማ ምክር ቤት ወጥተው በስራ ላይ እስካሉ ድረስ ተፈጻሚነት ሊኖራቸው ይገባል፤እንዲሻሻሉ ሃሳብ ከመስጠት ውጭ ፍርድ ቤቶች ውድቅ ሊያደርጓቸው አይገባም የሚል ክርክር የሚያነሱ አሉ፡፡ያም ሁኖ አሁን ባለው ሁኔታ ፍርድ ቤቶቹ ጉዳዮችን እያስተናገዱ ይገኛሉ፡፡

(ሐ) ለማህበራዊ ፍርድ ቤት የተሰጡ ደንብ መታለፍ ወንጀሎች

የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በወ/ህ/ቁ.790፣799፣800፣802፣803፣804፣፣805፣806፣807፣811፣813፣814፣815፣816፣817፣818፣819፣ 820፣822 ስር የተመለከቱትን ወንጀሎች የማየት ስልጣን የተሰጣቸው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 151/2000 አንቀጽ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም የስልጣን መደራረብ እንዳይኖር በጥንቃቄ መመርመር የሚስፈልግ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡

1.3.3 የስረ ነገረ ስልጣን /Material Jurisdiction/

የስረ ነገር ስልጣን ሲባል አንድ የወንጀል ዓይነት የሚመለከት ክስ በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት የሚወስን ስልጣን ነው፡፡ይህ ማለትም ጉዳዩ መታየት ያለበት በወረዳ /በመጀመሪያ ፍርድ ቤት/ ነው፣ በዞን /ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ወይስ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው የሚል ጥያቄ የሚመልስልን ነው፡፡

የክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና የፌዴራል ጉዳይ የሚያዩ ስለመሆኑ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ገለጻ የተመከተ ስለሆነ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ስለሆነም በቅድሚያ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን እንደሚከተለው ተመልክተነዋል፡፡

1.3.3.1 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሶስት እርከን የተከፈሉ ሲሆን እነዚህም፡-የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የጠ/ፍ/ቤት ተብለው ይታወቃሉ፡፡አዋጅ ቁጥር 25/1988

፤ይህንኑ አዋጅ ያሻሻለው አዋጅ ቁጥር 321/95 እንዲሁም የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ በስረ ነገር ስልጣን ክፍፍሉ ረገድ ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች ናቸው፡፡

(ሀ) **የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን**

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ወንጀሎች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 4(በፌዴራል መንግስቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎችና በጠቅላላ የገንዘብ ጥቅሞች ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ፣
- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 5(የሐሰት ገንዘብን በሚመለከቱ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 356-362) ፣
- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 6(በፌዴራል መንግስት ሰነዶች ላይ የሐሰት ስራ በመስራት የሚፈፀሙ ወንጀሎች) ፣
- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ ቁጥር 7(ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አግልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ፀጥታና ነፃነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች)፣
- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 9 መሰረት **የውጭ አገር ዜጎችን** እንዲሁም አንቀጽ 14 **(የፌዴራል መንግስት ንብረትን)** የሚመለከቱ ሁነው በስራ ላይ ባሉት ህጎች ለወረዳና ለአውራጃ ፍርድ ቤት የተሰጡ ወንጀሎች፤

ቀላል እምነት ማጉደል 675 የማይደፈር መብት ባለው የውጭ ዜጋ ቢፈጸም እና ይኸው ወንጀል በተራ የውጭ አገር ዜጋ ቢፈጸም በክልል ፍርድ ቤቶች በየትኛው ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር ናቸው?

- በህግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን እንደተጠበቀ ሁኖ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተመሞ ውስጥ በሚነሱ በስራ ላይ ባሉ ህጎች አወረዳ እና ለአውራጃ ፍርድ ቤት የተሰጡ ወንጀሎች

(ለ) የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ወንጀሎች ላይ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4

- ንዑስ ቁጥር 1 (በመንግስት ግዛት ሀገር ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች(በአዋጅ ቁጥር 321/95) የተሻሻለ ከወ/ሕግ ዓንቀፅ 238-260)፣

- ንዑስ ቁጥር 2 (በውጭ አገር መንግስት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 261-268) ፣
- ንዑስ ቁርጥ 3 (በሰው ልጆች መብት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወ/ሕግ ዓንቀፅ 269-283) ፣

ከዚህ ጋር በተያያዘ የግድያ፤በአካል ላይ ጉዳት ማድረስ የመሳሰሉት ወንጀሎች በሰው ልጆች መብት ሁኖ እያለ በወ/ሀ/ቁ.598 እና 585 በፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዴት ሊታዩ ቻሉ የሚል ክርክር ይነሳል፡፡

- ንዑስ ቁጥር 8 (የበረራ ደህንነትን በሚመለከቱ ወንጀሎች)፣
- ንዑስ ቁጠር 10 (አደገኛ እና አደንዛዥ እፆች ህገወጥ ዝውውርን የሚመለከቱ የሚመለከቱ ወንጀሎች)፣
- ንዑስ ቁጥር 13 (በተለያዩ ብሄሮች ብሄረሰቦች ጎሳዎች ኃይማኖቶች ተከታዮች ወይም የፖለቲካ ቡድኖች መካከል የተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፤(በአዋጅ ቁጥር 321/95 የተጨመረ)
- በአዋጅ ቁጥር አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 9 መሰረት የውጭ አገር ዜጎችን እንዲሁም አንቀጽ 14 (የፌዴራል መንግስት ንብረትን) የሚመለከቱ ሁነው በስራ ላይ ባሉት ህጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ ወንጀሎች)፤
- በህግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን እንደተጠበቀ ሁኖ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱ በስራ ላይ ባሉ ህጎች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ ሌሎች ጉዳዮች፡፡
- የፀረ ሽብር አዋጅ 652/2001 አንቀፅ 2(1) ...በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- የጸረ ሙስና አዋጅ ቁጥር 343/97 አንቀፅ 7.. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
- አዋጅ ቁጥር 501/98 የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አንቀጽ49 ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች
- አዋጅ ቁጥር 780/2005 በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርን በገንዘብ መርዳት ...ለፌ/ል ለከፍ/ፍ/ቤት

(ሐ) የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ስልጣን በክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲታይ በህግ ያልተወሰነ ስለሆነ ጉዳዩን በዝርዝር አልተመለከትነውም፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት ስልጣን በክልል ጠ/ፍ/ቤት በውክልና የሚታይ መሆኑ በህገ መንግስቱ በግልፅ የተመለከተ ስለሆነ ዳኞች ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የስልጣን ክፍፍል መርህን በመከተል ጉዳዮችን ማየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ለምሳሌ፡አበበ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን የመስመር ገመድ በሌሊት ቆርጦ ወስዷል ተብሎ ክስ ቢመሰረትበት ጉዳዩ የሚታየው በየትኛው ፍርድ ቤት ነው፡፡
- አለሙ ደሴ ከሚገኘው ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ የሚሰበሰበው ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለግል ጥቅሙ አዋለ ጉዳዩ የት ይታያልለ፡፡

1.3.3.2 **የክልል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን**

ጉዳዩ የፌዴራል ወይም የክልል መሆኑ ከተለየ በኋላ በየትኛው የክልሉ ፍርድ ቤት እንደሚታይ መወሰን ያስፈልጋል፡፡የፌዴራል ጉዳይ ከሆነ በህገ መንግስቱ በተሰጠው ውክልና መሰረት እንደወንጀሉ ሁኔታ በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በክልል ጠ/ፍ/ቤት የሚታይ ይሆናል፡፡እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊወሰድ የሚገባው የፌዴራል ጉዳይ ለማየት ውክልናው የሚጀምረው ከክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የወረዳ ፍርድ ቤቶች የፌዴራልን ጉዳይ የሚያዩበት የህግ መሰረት የለም፡፡

- የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 4 ፍርድ ቤቶች የሚያዩዋቸውና የሚፈርዱባቸው በዚሁ የስነ ስርዓት ሕግ በአንደኛው ሰንጠረዥ መሰረት ነው፡
- ይህ ሰንጠረዥ ግን ሕጉ ሲወጣ በነበረው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር መሰረተ የተዘጋጀ መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡የደርግ መንግስት ከተገረሰሰ በኋላ ግን የፍርድ ቤቶች ስልጣን በሚመለከት አንዳንድ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ለውጦች አንዱ ደግሞ ድሮ በአውራጃ ይታየ የነበረ የወንጀል ዓይነት በአሁኑ ጊዜ አውራጃ የሚባል ነገር ስለሌለ **ለወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቷል፡፡** እንዲሁም በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ወንጀሎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡
- የህግ ክፍል ማስታወቅያ ቁጥር 17/67 አንቀፅ 3 የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ያሻሻለ ሲሆን በተወሰኑ ወንጀሎች የስልጣን ለውጥ ተደጓል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል ህጉ

በግልፅ ባልተመለከቱ ወንጀሎች ሁኖ በእስር ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ከሆነ ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ከአስር ዓመት በታች የሚያስቀጣ ከሆነ ግን ጉዳዩ የሚጣየው በወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡

- የሙስና ወንጀሎች በተለየ ሁኔታ በፌዴራል አዋጅ ቁጥር 343/97 አንቀፅ 3 እና በአብክመ አዋጅ ቁጥር 93/96 መሰረት የሙስና ወንጀሎች የፌዴራል ጉዳይ ከሆነ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልል ጉዳይ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንደሚታይ ተመልክቷል፡፡
- የተሰራው ወንጀል በወንጀል ሕግ የሌለ ቢሆን፣ እንበል አንድ ሰው በሌላ አዋጅ የወጣ ድንጋጌ ቢጥስ የትኛው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንዳለው የሚወስነው ለጥፋቱ የተመደበውን ከፍተኛ የቅጣት ወሰን በመመልከት ነው፡፡ አሁን ያለው የፍርድ ቤት አወቃቀር መሰረት አድርግን ስናየው የሚያስቀጣው ከአስር ዓመት በታች ከሆነ ለወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ከአስር ዓመር በላይ ከሆነ ደግሞ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ የህግ ክፍል ማስታወቅያ ቁጥር 17/67 አንቀፅ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡
- የመንግስት ደን በተመለከተ የወጣው አዋጅ ቁጥር 542/99 ደን የቆረጠ የደን ውጤት የወሰደ 1-5፣ በእሳት የለኮሰ 5-15፣የስልጣን ልዩነት አላቸው

1.3.4 ከባቢያዊ ስልጣን (Local Jurisdiction)

ይህ ዓይነት ስልጣን የት ወረዳ ወይ ዞን ያለ ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የሚለውን ነገር በማየት የሚወሰን ነው፡፡ እንደ ወንጀለ ዓይነት ክሱ መታየት ያለበት በወረዳ ፍርድ ቤት የሆነ እንደሆነ በየተኛው ኣከባቢ ያለ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው ክሱ መታየት ያለበት የሚለውን ነገር የሚወስን ነው፡፡

- የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 6 እንደሚያመላክተው በተለያዩ ኣከባቢ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 99-107 የተወሰነላቸው ቦታ መሰረት ኣድርገው የዳኝነት ተግባራቸውን የማከናወን ስልጣን እንዳላቸው ነው፡፡
- በመርህ ደረጃ ማንኛውም የወንጀል ክስ ወንጀለ በተፈፀመበት ኣከባቢ በሚገኘው ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የወ/ወ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.99 ይደነግጋል፡፡
- በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀለ የተፈፀመበትና የወንጀለ ውጤት የታየበት ኣካባቢ የተለያየ የሚሆንበት ኣጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ይህም ማለት ወንጀለ የተፈፀመው

በአንድ ወረዳ ወይም ዞን ሲሆን የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ወረዳ ወይም ዞን ሊሆን ይችላል፡፡

- በዚህ ጊዜ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ማለትም ወንጀሉ በተፈፀመበት አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ወይም የዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት ወይም የወንጀሉ ውጤት በታየበት አከባቢ የሚገኝ የወረዳ /ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የክልል ስልጣን (Local Jurisdiction) አላቸው ማለት ነው፡፡

<u>ለምሳሌ፡-</u> አንድ የሰሜን ሸዋ ዞን ነዋሪ ሰውን በመግደል አስቦ ደቡብ ጎንደር ለሚኖረው ሰው የተመረዘ ምግብ ቢልክለትና ግለሰቡ በዚሁ ምክንያት ቢሞት ጉዳዩ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊሰማ ይችላል፡፡

- ያም ብቻ ሳይሆን ወንጀሉ የተፈፀመው በአንድ የክልል መስተዳደር፤ የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ክልል መስተዳደር የሆነ እንደሆነም በአንዳቸው ክልል መስተዳደር ስር የሚገኝ የስረ ነገር ስልጣን ያለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ኣይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን ነው፡፡
- ቀጥሎ የሚነሳ ጉዳይ ደግሞ ወንጀሉ የት እነደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆንስ ክስ መሰማት ያለበት የት ነው የሚለውን ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102(ሀ) ያሰቀመጠው መፍትሄ አለ፡፡ በአንቀፁ እንደተመለከተው ወንጀሉ የት እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን ክሱ ስልጣን ባለው በአንድ ስፍራ በሚገኝ ፍርድ ቤት ሊሰማ እንደሚቻል ነው፡፡

<u>ለምሳሌ፡-</u> አንድ ሰው የወንጀል ሕግ ዓነቀፅ 665ን በመተላለፍ አንድ በሬ ቢሰርቅ ወንጀሉ መሰማት የሚገባው በወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ነገር ግን ተከሳሹ ከየት እንደሰረቀው ለይቶ ባያውቅና ከዳንሻ ወረዳ ወይም ከፀገዴ ወረዳ ከሁለቱ አንዱ መሆኑ ግን ግልፅ ቢሆን ተጠርጣሪው በዳንሻ ወይም በፀገዴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊከሰስ ይችላል፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀሉ በከፊል ግማሹ በአንድ ስፍራ ግማሹ ደግሞ በሌላ ስፍራ ሲፈፀም (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102(ለ) ወይም ወንጀሉ በብዙ ስፍራዎች ያለማቋረጥ ሲፈፀም (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.102(ሐ) ወይም ወንጀሉ በልዩ ልዩ ቦታዎች በተሰሩ ልዩልዩ ተግባሮች የተፈፀመ ሲሆን (ቁ.102(መ)) ክሱ በአከባቢው ካሉት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማንኛውም ሊሰማ ይችላል፡፡
- በቁ.103 መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ቢሆን ተጠርጣሪው ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው ወይም ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ስፍራ ውስጥ

ክሱን ለመስማት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክሱ ይታያል፡፡ ተጠርጣሪው ወንጀል የፈፀመበት ሰው ወይም ሌላ ነገር (ንብረት) በስፍራው ካለፈ ወንጀሉ በዛው ስፍራ ባይፈፀምም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በነገሩ ሊፈርድ እንደሚችል ነው፡፡

<u>ምሳሌ 2</u>፡- በኮምቦልቻ ወረዳ በመኪና የተጫነ የንግድ እቃ በደብረሲና ኣቋርጦ ደብረብርሃን ሲደርስ ቢሰረቅ እቃው በሶስቱም ወረዳዎች ውስጥ ስላለፈ ወንጀለኛው ከሶስቱ ወረዳ ፍርድ ቤቶች በማንኛውም ሊከሰስ ይችላል፡፡

- አንድ ወንጀል ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ወይም ኤሮፕላን ውስጥ ቢፈፀም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈፀመ ይቆጠራል ይላል (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.104)፡፡ ይህ ቁጥር ክሱ በየትኛው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው አይገልፅም፡፡ ሆኖም ቁ.107 ከቁ.100 እስከ 104 የተመለከቱትን ዓይነት ወንጀሎች ሁሉ ክሱ በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት ዓቃቤ ሕጉ ሊወስን እንደሚችልና ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንደሚኖረው ይገልፃል፡፡ ስለዚህ አንድ ክስ በብዙ ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል ሲሆን በየትኛው ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ዓቃቢ ሕጉ ይወስናል ማለት ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኤሮፕላን በሱዳን ላይ ሲበርና በወረዳ ፍርድ ቤት መታየት የሚገባው ወንጀል በኤሮፕላኑ ውስጥ ቢፈፀም ጉዳዩ ዓቃቤ ሕግ በሚመርጠው በማንኛውም የኢትዮጵያ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊታይ ይቻላል፡፡

ክስ ማዛወር

ከክልላዊ ስልጣን ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነገር ቢኖር አንድ ክስ ካንድ ነገሩን ለማየት ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት **የመዛወሩ ጉዳይ ነው** (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 106) ፡፡

- ባለጉዳዩ ጉዳዩን በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይለት ሲፈልግ ማመልከቻውን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንዳለበት የተጠቀሰው የሕጉ ቁጥር ይደነግጋል፡፡ ማመልከቻውን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከተቀበለው ጉዳዩ ክሱን ለማየት ስልጣን ወደ ኣለው ፍርድ ቤት ወይም ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይዛወራል፡፡ በዚህ አኳኃን ጉዳዩ በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታይ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤት ራሱ ተቀብሎ ሊሰማው ወይም ወደ ሌላ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊያዛውረው ይችላል፡፡

- ይህ ዓንቀፅ ድሮ ለነበረው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት ታሳቢ በማድረግ የተቀረፀ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ላለውን የፌዴራል አወቃቀር ስርዓት እንዳለ የሚያገለግል አይመስልም፡፡
- ፍርድ ቤቶች በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ የተዋቀሩ በመሆናቸው የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄም ይህንን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በሆነው ጉዳይ ላይ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጥያቄው መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ክልሎች በውክልናቸው መሰረት በሚያዩት ጉዳይ ላይ ከሆነ ደግሞ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል ማለት ነው፡፡
- እንዲሁም የክልል ጉዳይ ሲሆን ሁለት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ይኸውም የወረዳ ፍርድ ቤት በያዘው ጉዳይ ላይ ሲሆን ጥያቄው ለሚመለከተው የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤት በያዘው ጉዳይ ላይ ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባዋል፡፡

- የሚመለከተው ፍርድ ቤት አንድ ክስ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የቀረበለትን ማመልከቻ የሚቀበልበት አራት ሁኔታዎች እንዳሉ ቁጥር 106 ያመለክታል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) **ዝቅተኛው ፍርድ ቤት በልዩ ልዩ ምክንያቶች አድልዎ የሌለበት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት እንደማይችል ግልፅ ሲሆን ፣**

ለ) **ክሱ በጣም አስቸጋሪና ከባድ የሆነ ለውሳኔ የሚያዳግት የሕግ ጉዳይ ሲኖርበት ፣**

ሐ) **የክሱ መዛወር ለባለጉዳዩችና ለምስክሮች በቦታው ቅርበትም ሆነ በሌላ ምክንያት ምቹ ወይም ተፈላጊ ሲሆን ፣ እና**

መ) **በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው በክሱ መዛወር ብቻ ሲሆን ወይም የክሱ መዛወር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ- ስርዓት የተፈቀደ ሲሆን ነው፡፡**

II. ክስን ስለመስማት

2.1 ክስ ከመሰማቱ በፊት መጠናቀቅ ያለባቸው ዝግጅቶች

የወንጀል ክስ ሳይቀርብ የወንጀል ክስን የመሰማት ሂደት እንደማይኖር የታወቀ በመሆኑ የክስ ማመልከቻ ተዘጋጀቶ መቅረብ ይገባዋል፡፡

- የግል ክስ በተመለከተ ቀደም ሲል በቀረበው ርዕስ ገለፃ የተደረገለት በመሆኑ ምክንያት ታለፈ ሲሆን ወጣት አጥፊዎችን በተመለከተ የሚቀርብ ክስ ግን ወደ ፊት ራሱ በቻለ ርዕስ የሚቀርብ በመሆኑ በዚህ ርዕስ የሚዳሰስ አይሆንም፡፡ በመሆኑም
- የክስ ማመልከቻው የደረሰው ፍርድ ቤት ክሱን የማየት ስልጣን እንዳለው ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ክሱ ስልጣን ለሌው ፍርድ ቤት የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ክሱን አልቀበልም በማለት ዓቃቤ ሕግ ክሱን ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ በክስ ማመልከቻው ላይ መግለፅ እንዳለበት የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 110 ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ወንጀሉ የስርቆት ወንጀል ከሆነ ግን ክሱን አልቀበልም ማለት እንደሌለበት እና ጉዳዩን ማየት እንዳለበት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ግንጋጌ በሁለተኛ ፓራግራፍ ተመልክቷል፡፡

የስርቆት ወንጀል (የወ/ሀ/ቁ.665) በስህተት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለኝም ብሎ ለወረዳ ፍርድ ቤቱ የማይመልስበት ምክንያት ምንድን ነው?

- ፍርድ ቤት የቀረበለት ክስ ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የክሱ ግልባጭ ወድያውኑ ለተከሳሽ ሊልክለት እንደሚገባም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.109 (4) ይደነግጋል፡፡
- ይህ የክስ ግልባጭ የማግኘት መብት በኤፌዲሪ ሕገ መንግስት እውቅና አግኝቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ ዓንቀፅ 20 (2) የተመለከተ ሲሆን፤ የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በፅሑፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልፅ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የተከሰሱ ሰዎች የክሱ ግልባጭ (በፅሑፍ) ሊደርሳቸው ይገባል ብቻ ሳይሆን የክሱ ማመልከቻ በበቂ ሁኔታ ዝርዝር ነገሮችን መያዝ እንዳለበትና ተከሳሾች የተከሰሱበት ጉዳይ በሚገባ እንዲረዱ የሚያስችላቸው መሆን እንደአለበት ነው፡፡

የክስ ማመልከቻ ለተከሳሽ እንዲደረሰው የሚደረገበት ምክንያት ፣በዋነኛነት

- በክሱ የተገለፀው ዝርዝር ነገር አይቶ ለመከላከል ዝግጅት እንዲያደርግ ስለሚያስችለው፣ክሱ እንዲደርሰው ብቻ ሳይሆን ክሱን አንብቦ እንዲገነዘበው ጭምር ክሱ ከመሰማቱ በፊት ቀደም ብሎ ሊደርሰው የሚገባ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

ይሁን እንጂ በተግባር በተለይም በተዘዋዋሪ ችሎት ወቅት የክስ ማመልከቻ በችሎት የሚሰጥበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ምሳሌ፡-አቶ ምንተስኖት በከባድ ግድያ ሙከራ ወንጀል ተከሶ ክሱ ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረቡ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመስማት ሶስት ቀጠሮዎችን እንዲቀይር ተግዷል፡፡አቶ ምንተስኖት በተንታ ወረዳ በሚያስችለው የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት በአራተኛው ቀጠሮ በፖሊስ ታጅቦ ቀረበ ፍርድ ቤቱ ክሱን ለመስማት በዝግጅት ላይ እያለ አቶ ምንተስኖት የክስ ማመልከቻው አልደረሰኝም፤ስለሆነም ክሱ ዛሬ ሊሰማ አይገባም፡፡የክሱ ማመልከቻ ለመመልከት እና ከጠበቃ ጋር ለመመካከር ጊዜ ይሰጠኝ በማለት ተከራከረ፡፡ዐ/ህግ ቀርቦ ተከሳሽ በፍለጋ የተገኘ በመሆኑ እና የተዘዋዋሪ ችሎቱ መርሃ ግብር ዛሬ የሚጠናቀቅ በመሆኑ ክሱ ሊሰማ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ እርሰዎ የችሎቱ ዳኛ ቢሆኑ ምን አቋም ይወስዳሉ፡፡

- የክስ ግልባጭ ለተካሰሸ የሚላክለት ክሱን ለማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ነገሩ የሚሰማበትን ቀን ከወሰነ በኋላ ስለሚሆን መጥሪያንም አብሮ የሚላክለት ይሆናል፡፡
- ዓቃቤ ሕጉም ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንዲቀርብ መጥሪያ ይላክለታል፡፡
- ፍርድ ቤቱ ክሱ የሚሰማበት ቀን ሲወስን እንዲሁ በግምት ሳይሆን ተከሳሹ የሚገኝበት ቦታ ቅርበትና ርቀት፤ ምስክሮች የሚገኙበትና ለመቅረብ የሚወስድባቸው ጊዜ፤ የፍርድ ቤቱ የመዝገብ ብዛት ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት፡፡
- ይህም የቀጠሮ ቀን ስለመወሰንና ስለመጥሪያ አላላክ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.123 ላይ ተመልክቷል፡፡
- ክሱ የሚሰማበት ቀን እንደተወሰነ ሌላ መደረግ ያለበት ዐ/ህጉና ተከሳሹ የማስረጃቸውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር ማቅረብ ነው ያለበት መሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.124 ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡
- የማስረጃው ዓይነት የክሱ ፍሬ ነገር በቀጥታ ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቁ ምስክሮች እና/ ወይም ልዩ እውቀት ያላቸው ሰዎች (ኤክስፐርቶች) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ምስክሮች ነገሩ በሚሰማበት ቀን ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን መስጠት እንዲችሉ በፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር በኩል መጥሪያ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

- **የማስረጃው ዓይነት ሰነድ ወይም ኢግዚቢት ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በማድረግ (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.124 (2)) የሰነድ ማስረጃው ግልባጭ ለተከሳሹ ከክሱና ከመጥሪያው ጋር እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡የማስረጃው ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ማድረግ በሕገ መንግስቱ ዐንቀፅ 20(4) ላይ እውቅና ያገኘ መብት ነው፡፡ይህ ድንጋጌ የተከሰሱ ሰዎች "የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት መብት አላቸው" በሚል ተደንግጓል፡፡**
- **የዚህ መብት ፋይዳ ተከሳሹ የተመሰረተበት ክስና ክሱን ለማስረዳት የቀረበበት ማስረጃ በቂ ጊዜ አግኝቶ እንዲያየውና እንዲመረምረው ያስችለዋል፤ የመከላከል ዓቅሙ እንዲጎለብት ያስችለዋል፡፡ተከሳሹ የሰነድ ማስረጃ ያለው እንደሆነም ግልባጭ ለዓ/ሕጉ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ስለዚህ ሁለቱ ወገኖች የማስረጃ ግልባጭ ልውውጥ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡**
- **ከዚህ አንፃር ሲታይ ክስን ለመስማት ዝግጅት ማድረግን በተመለከተ በኮመን ሎ** (Common law) **ስርአት በሚከተሉ አገሮች እና ሲቪል ሎ**(Continental / civil law) **ልዩነት ይታያል፡፡**
- **በኮመን ሎ የሕግ ስርዓት ክስ መሰማት ከመጀመሩ በፊት ፍርድ ቤቱ ክስና የተከራካሪ ወገኖች የማስረጃ ዝርዝር ብቻ ነው የማግኘትና የማየት እድል ያለው፡፡አልፎ አልፎ ግን ጉዳዩ የሚሰማው በጁሪ ከሆነ (እንግሊዝ) ፍ/ቤቱ የዐ/ሕግ ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡት የምስክርነት ቃል የሚያገኝበት ሁኔታ አለ፡፡በተጨማሪም አስቀድሞ ሰነዶችን የማየቱ ልምድ አነስተኛ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በዳኛ መሪነት ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በቅድመ ክስ ንግግር** (Pretrial Conference) **የማስረጃቸውን ይዘት ግልፅ የሚያደርጉበት ሁኔታ እየታየ ነው፡፡**
- **በሲቪል ሎ የሕግ ስርዓት ያለ አሰራር ግን ፍ/ቤቱ የክስ ሂደት መሰማት ከመጀመሩ በፊት የክስ ማመልከቻና ሁሉም የምርመራ ሰነዶችና ከዛ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች ከመዝገቡ ስለሚያያዙ ዳኛው ማስረጃውን ለመመርመር እና ክሱ ለመሰማት ዝግጅት እንዲያደርግ እድል ይሰጠዋል፡፡ፍ/ቤቱ ሰነዶቹ ከደረሱት በኋላ የማጣራትና የመለየት ተግባር ያከናውናል፡፡ምስክሮችንና ተከሳሽን ለመጠየቅ የሚያስችለው ዝግጅት ያደርጋል፡፡ተከራካሪ ወገኖችም ያቀረቡትን ሰነድ በመለዋወጥ ያጠኑታል፤ ለቀጣይ ክርክር ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ይህ አሰራር ማስረጃን ለመመርመር እየተባለ አላስፈላጊ**

ቀጠሮ እዳይሰጥና ጉዳዩ እንዳይጓተት አስተዋፅኦ ከማድረጉ በተጨማሪ የተዘበራረቁ ነገሮች በማስወገድ የነጠረ የክስ መስማት ሂደት እንዲኖር ያግዛል፡፡

2.2 ስለ ክስ መሰማት አጀማመር (Opening of hearing)

ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀንና ሰዓት ክሱን ለመስማት ፍርድ ቤቱ ማስቻል አለበት፡፡ የተከሳሹን ወይም የተበዳዩን የግል ህይወትና ሞራል፤ የህዝቡን የሞራልና የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዝግ ችሎት እንዲታይ ካልወሰነ በቀር ክሱ በግልፅ ችሎት (Public trial) መታየት ይኖርበታል (የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 20 (1) ፡፡

የክስ መሰማት ሂደት በግልፅ ችሎት እንዲካሄድ መደረጉ፡-

- ችሎቱን የሚከታተሉ ወገኖች ዳኞች ገለልተኛነታቸውን ጠብቀው ባለጉዳዮችን በእኩልነት እያዩ ሂደቱ እየመሩ ስለመሆናቸው እንዲያረጋግጡ እድል ይሰጣል፡፡
- ችሎቱን የሚከታተሉ ወገኖች ግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት ማስረጃንና የሚሰጠውን ፍርድ ይዘት ለመገምገም ያስችላቸዋል፡፡
- በአጠቃላይ ዳኞች ነፃነታቸውን ጠብቀው ሕግንና ህሊናቸውን መሰረት አድርገው ምን ያህል የዳኝነት ስራቸውን እያከናወኑ እንዳሉ ህዝቡ እንዲገነዘብ ያስችለዋል፡፡ ይህም በህዝብ አመኔታን(public confidence) ያተርፋል፡፡
- ተከሳሹ ክሱን እንዲሰማና መከላከል እንዲችል በችሎት በአካል መገኘት አለበት፡፡
- ተከሳሽ በሕግ የተቀመጠለት መብት በአግባቡና በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀምበት እና በአግባቡ ክርክሩን እንዲያካሂድ በጠበቃ መታገዝ ተገቢ በመሆኑ ጠበቃ ካለው ከጠበቃው ጋር እንዲቀርብ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ተከሳሽ በግሉ ጠበቃ የመቅጠር አቅም የሌለው መሆኑ ከታወቀ እና ያለጠበቃ ቢከራከር ፍትህ ይጓደላል ተብሎ የሚገመት ከሆነ በመንግስት ወጭ ጠበቃ እንዲመደብለት የማድረግ መብት ያለው መሆኑ በህገ/መን/አንቀፅ 20(5) ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡በተለምዶ ፍርድ ቤቶች የመንግስት ጠበቃ እንዲቆምላቸው የሚያደርጉት በግድያ ወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች ነው፡፡ይሁን እንጂ ህገ መንግስቱ በመንግስት ወጭ ጠበቃ ለማግኘት የወንጀሉ አይነት እንደመስፈርት አላስቀመጠም፡፡መስፈርቶቹ ተከሳሹ የአቅም ማጣት እና ፍትህ ይጓደላል ብቻ በመሆናቸው ከግድያ ወንጀል ውጭ ያሉት ወንጀሎች በተመለከተም ተከሳሽ ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

- ተከሳሽ ጠበቃ እንደሌለው ገልፆ መንግስት እንዲመድብለት ከጠየቀ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ተከሳሹ የመንግስት ጠበቃ ሊመደብለት የሚገባ መሆኑ አለመሆኑን መመርመር አለበት፡፡
- እዚህ ላይ ተከሰሽ ጠበቃ ለማቆም ዓቅም እንዳለው ወይም እንደሌለው ፍ/ቤቱ እንዴት ማረጋገጥ ይችላል የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡
- ፍ/ቤቱ ይህንን ለመመርመር የግድ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ስልጣን አለው፡፡አንዳንድ ጊዜም ከተከሳሹ ገቢና ዓቅም ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቱ ለሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ተከሳሹ በመሃላ ስር ሆኖ የሚሰጠው መረጃ በቂ የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡
- ከዚህ ጋር በተያያዘ የከ/ፍ/ቤቶች ተዘዋዋሪ ችሎት በወረዳ ሲያስችሉ የተከላካይ ጠበቃ እጥረት ሲኖር ዳኞች በተከላካይ ጠበቃነት ቀርበው ሲከራከሩ ይስተዋላል፡፡ይህ ሁኔታ ከህግ አግባብ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ውይይት ያስፈልገዋል፡፡
- ሌላ መነሳት ያለበት ጥያቄ የቀረበበት ወንጀል ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ተከሳሹ በጠበቃ ካልተከራከረ ፍትሕ ሊጓደል ይችላል ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ **ተከሳሹ ጠበቃ አልፈልግም ፤ በራሴ እከራከራለሁ ቢል ያለ ጠበቃ መከራከር መብት ነውና ፍ/ቤቱ ምን ማድረግ አለበት የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ሁለት የተለያዩ መልሶች ሊቀርቡበት ይችላሉ፤**

(1) በአንድ በኩል በጠበቃ መከራከር መብት መሆኑን በሕግ እስከተደነገገ ድረስ በመብቱ መጠቀም ወይም አለመጠቀም የሚችለው ባለመብቱ ራሱ በመሆኑ በመብቴ አልጠቀምም፤ አልፈልግም ካለ ከፈቃዱና ፍላጎቱ ውጭ የሚደረግ ነገር ስለማይኖር ነገሩ እዛ ላይ ያቆምና በመረጠው መንገድ (ያለ ጠበቃ) ሊከራከር ይገባል የሚል ሲሆን፤

(2) በሌላ በኩል ደግሞ በጠበቃ መከራከር ግዴታ ባይሆንም (መብት ነው) ለፍትሕ ሲባል ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በራሱ እንዲከራከር ከመፍቀዱ በፊት ያለጠበቃ መከራከር

- የክስ መስማት ሂደት ሲጀመር ሌላ ትኩረት የሚሻ ነጥብ አስተርጓሚ የመመደብ ጉዳይ ነው፡፡ ችሎቱ የሚካሄደው ለተከሳሹ በማይገባው **ቋንቋ ከሆነ ፍ/ቤቱ በመንግስት ወጪ አስተርጓሚ ሊመድብለት ይገባል (ሕገ መንግስት አንቀፅ 20 (7) እና የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.126 (2) ይመለከተዋል)፡፡አስተርጓሚ** የሚመደበው ተከሳሹ ሲያመለክት ወይም ተከሳሹ ባያመለክትም የችሎቱን ቋንቋ የማይገባው መሆኑን

ፍ/ቤቱ ሲረዳው ነው፡፡ቋሚ የፍ/ቤት አስተርጓሚ ካለ የተከሳሹን ቋንቋ የሚረዳ አስተርጓሚ ፍ/ቤቱ ይመድባል፡፡ቋሚ አስተርጓሚ ከሌለ ወይም ያሉት አስተርጓሚዎች የተከሳሹን ቋንቋ የማይረዱ ከሆነ ለተከሳሹ ወይም ለዐ/ህጉ ወይም ለግል ተበዳዩም ጭምር ዘመድ (የስጋ ወይም የጋብቻ) ያልሆነ ችሎታ ያለው ሌላ ሰው ፍ/ቤቱ መርጦ መመደብ አለበት፡፡ሕጉ በግልፅ ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም አስተርጓሚው ክርክሩን መተርጎም ከመጀመሩ በፊት በእውነት ለመተርጎም መማል አለበት፡፡

የተከሳሽ አቀራረብ

የተከሳሽ ኣቀራረብስ እንዴት መሆን አለበት የሚለውን ስናይ ደግሞ አደገኛ ለመሆኑ ወይም የሓይል ድርጊት የሚፈፅም ለመሆኑ ወይም ለማምለጥ የሚሞክር መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ምክንያት ከሌለ በስቀር በሰንሰለት ታስሮ መቅረብ እንደሌለበት የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.127 ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ተከሳሹ ችሎት ፊት እንደቀረበ በሳጥን ውስጥ ገብቶ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ በሳጥን ውስጥ እንዲገባ የሚደረግበት ዋና ምክንያት ለጥበቃ እንዲመች ሲሆን፤ ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎች ተከሳሽን በቀላሉ እንዲለዩትም ሊጠቅም ይችላል፡፡

የተከሳሹ በሳጥን ውስጥ መግባት ተከትሎ መከናወን ያለበት ነገር ቢኖር የተከሳሹ ማንነት ማረጋገጥ ነው፡፡በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 128 እንደተመለከተው “ተከሳሹ በሳጥን ውስጥ ገብቶ ከቆመ በኃላ ማንነቱ፤ ዕድሜውና ስራዉ መረጋገጥ አለበት” ይላል፡፡ እዚህ ላይ ማንነት የሚል ቃል በሰፊው ካልተተረጎመ በስተቀር ስም እና እድሜው እናስራው ብቻ ለማመልከት የተቀመጠ ነው የሚመስለው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ተከሳሽ ለፍ/ቤት መግለፅ ያለበት ስሙ፤ ዕድሜውና ስራው ብቻ ሳይሆን፤ ዖታው፤ አድራሻው፤ የትምህርት ደረጃውና የቤተሰቡ ሁኔታ (ያገባ ወይም ያላገባ መሆኑ፤ ልጆች ያሉት ወይም የሌሉት መሆኑ ወዘተ) ጭምር ነው፡፡

ስም፤ዕድሜ፤ስራ አድራሻ፤ዖታ፤የትምህር ደረጃ፡የትዳር ሁኔታ፤የቤተሰቡ ሁኔታ ሊጠቀስ ይገባል፡፡

2.3 ክስ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ እርምጃ

ዐ/ህግ የክስ ማመልከቻ ካቀረበ በኃላ ፍ/ቤቱ ክሱን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ ዐ/ህግ ተከሳሽ እንዲቀርቡ መጥሪያ እንደሚልክላቸውና ተከሳሽ በአካል ቀርቦ መከራከር አስፈላጊ መሆኑን ከላይ ተመልክቷል፡፡ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት እያለ በቀጠረው ዕለት ያልቀረበ

እንደሆነ ፖሊስ በእስር እንዲያቀርበው ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንደሚሰጥም አይተናል (ቁ.125 እና 160 (2))፡፡ በእስር እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት የቀረበ እንደሆነ የክሱ መስማት ሂደት ይቀጥላል፡፡

- **ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ ፖሊስ ተከሳሹን አስሮ ሲያቀርበው ይዘወተራል፡፡በዋስ ላለ ተከሳሽ መጥሪያ ማድረስ በቂ ነው፡፡መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ግን ታስሮ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ስለሆነም በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ በዋስ ያለን ተከሳሽ አስሮ ማቅረብ ተገቢ ባለመሆኑ ዳኞች የእርምት እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል፡፡**

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ ፖሊስ ተከሳሽን ፈልጎ በእስር እንዲያቀርብ የተሰጠው ትእዛዝ ሳይሳካለት ቢቀርስ (ፈልጎ ቢያጣውስ) የሚወሰድ እርምጃ ምንድን ነው የሚል ይሆናል፡፡ ይህ ጥያቄ **በሁለት መንገድ ሊመለስ የሚችል** ነው፡፡ ይኸውም፡-ተከሳሽ በቂ ባልሆነ ምክንያት ክስ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ እና ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ህጉ የሚፈቅድ እንደሆነ(ቁ.160-163) በሌለበት ክሱ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ሊያዘዝ ይችላል፡፡ ሁለተኛው ህጉ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የማይፈቅድ ከሆነ ግን ዐ/ህግ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብቱ ተጠብቆ መዝገቡ የሚዘጋ ይሆናል፡፡ጉዳዩ በይርጋ ካልተቋረጠ ተከሳሽ በተገኘ ጊዜ ዐ/ህግ መዝገቡን ከማንቀሳቀስ የሚያግደው ህግ የለም፡፡(የፌ/ስ/ሰሚ ችሎት ቅፅ 10 የመ/ቁ.45572)

- **አንድ ጉዳይ በሌለበት ስለማየት እና በሌለበት የተሰጠ ውሳኔን ስለማስነሳት በተመለከተ በተለየ ርዕስ ወደ ፊት የምንመለከተው ስለሆነ በዚህ ርዕስ አልተዳሰሰም፡፡**

2.4 ክስን ስለ ማሻሻል እና ስለ ማንሳት

2.4.1 ክስን ስለ ማሻሻል

አንድ ክስ ፍርድ /ውሳኔ/ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በባለጉዳዩች ማመልከቻ በቀረበለት ጊዜ ክስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ **በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.** 119 **ተደንግጎ** ይገኛል፡፡ይህ የሕግ ቁጥር እንደሚያመለክተው በተከሳሹ ላይ በቀረበው ክስ ዋና ስህተት የተገኘ ሲሆን ወይም ያልተጠቀሰ ነገር ሲገኝና ይኸውም ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ እንደ ነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችል የሚገልፅ ነው፡፡ **ስለዚህ የክስ ማሻሻል ውጤት በክሱ ላይ ለውጥ ማድረግ ወይም መጨመር ወይም አዲስ ክስ ማዘጋጀት ነው፡፡**

በዚህ የሕግ ቁጥር ዙርያ ሲያከራክር የነበረና አሁንም እያከራከረ ያለው ነጥብ ክስን የማሻሻል ዓላማ በሚመለከት ነው፡፡

- (1) ክስን የማሻሻል ዓላማ ተከሳሹን ሊያሳስትና ሊጎዳ የሚችል ስሕተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ (ለተከሳሹ ጥቅም ሲባል የሚደረግ) ነው የሚል ክርክር እየተነሳ እንዳለሁሉ፤
- (2) ለተከሳሹ ጥቅም ብቻ ተብሎ ሳይሆን ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የማያስችል ስህተት ሲገኝም ጭምር ክስ መሻሻል አለበት ብለው የሚከራከሩ አሉ፡፡
- የመጀመርያው ሓሳብ የሚደግፉ ሰዎች ለክርክራቸው መሰረት አድርገው የሚወስዱት ዓንቀፅ 119 ብቻ ሲሆን፤ ሁለተኛው አመራሩ የሚደግፉ ደግሞ ቁ.119 ከቁ.118 በማጣመር ሊታይ ይገባል ይላሉ፡፡ቁ.118 እንደሚያመለክተው “... ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው አስፈላጊ ነገር ካልሆነ ወይም ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ተከሳሹን ያሳሰተው ካልሆነ ወይም በዚህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል ካልሆነ በቀር እንዲህ ያለ ስህተት ወይም ሳይጠቀስ የቀረው ነገር ክሱን ዋጋ አያሳጣውም፡፡” ይላል /ሰረዝ የተጨመረበት/፡፡
- ስለዚህ ከሁለቱ ቁጥሮች አገላላፅ ክስን የማሻሻል ዓላማ በአንድ በኩል ተከሳሹን እንዳያሳስትና እንዳይጎዳ ሲሆን፤በሌላ በኩል ደግሞ ውጤቱ ተከሳሽን የሚጎዳ ቢሆንም ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት ክሱን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም ሊሻሻል እንደሚገባ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡

በተግባር እንደሚታየውም ሁለቱ የአተረጓጎም መንገዶች እየተሰራባቸው ይገኛል፡፡

- ስለዚህ የወንጀል ፍትሕ ስርዓት ዓላማ የመንግስትና የህዝብ ጥቅም ፤ በወንጀሉ የተጎዳ ሰውን እና የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ በመሆኑ በክስ ማሻሻል ሂደትም የተከሳሹን መብት ለማስጠበቅ /ለመጠበቅ/ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ የፍትሕ ስርዓቱ ለማሳካት ሲባልም ሊደረግና ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ነው፡፡

(ወደ ከበደ ወንጀል ለመቀየር ክስ ማሻሻል ይቻላልን?)

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለምሳሌ የግል ተበዳይ ከመሞቱ በፊት ተከሳሽ በግድያ ሙከራ ተከሶ ከነበረ እና ክሱ እየተሰማ ባለ ጊዜ ተግል ተበዳይ ቢሞት ዐ/ህግ ክሴን ላሻሽል ብሎ ቢቀርብ ክሱን ማሻሻል ተገቢ ይሆናል የሚል እምነት አለን፡፡የግል ተበዳይ ሞቶ እያለ ተከሳሽን በግድያ ሙከራ መቅጣት ፍትሃዊ አይሆንም፡፡ስለሆነም ወደ ከበደ ወንጀል ለመለወጥም ክስ የሚሻሻልበት እድል ያለ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሌላው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ክስን የማሻሻል ጥያቄ መቅረብ ያለበት"...ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ..." መሆኑን ቁጥር 119 ያመለክታል፡፡ ይህ ድንጋጌ የተፋጠነ ፍትሕ እንዳይሰጥ ሂደቱ የተጓተተ እንዲሆን ምክንያት አይሆንም ወይ? የሚል ነው፡፡

ክስን የማሻሻል ውጤት ምን እንደሆነ ወይም ክስ እንዲሻሻል ከተፈቀደ በኋላ መደረግ ያለበት ነገር ምን እንደሆነ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.120 እና 121 ተደንግገዋል፡፡ድንጋጌዎቹ እንደሚያመለክቱት ዓ/ሕግ ያቀረበውን የተሻሻለ ክስ ግልባጭ ለተከሳሹ እንዲደርሰው ይደረግና የክስ መሰማቱ ሂደት እንደ አዲስ ይጀምራል፣ዓ/ሕግ ማስረጃውን ያሰማል፣ ተከሳሽም የመከላከያ ማስረጃ ካለው ያቀርባል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ስነ ስርዓት ሳይፈፀም የሚቀርበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

ምሳሌ በአንድ ወረዳ ፍ/ቤት በስርቆት ወንጀል ተከሰው የነበሩ ተከሳሾች ለቀረበባቸው ክስ ክደው ስለተከራከሩ ዓ/ሕግ ምስክሮቹን አቅርቦ ያሰማል፡፡ ፍ/ቤቱም ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ የለንም ብለው ያስመዘግባሉ፡፡ ከዛ በኋላ ዓ/ሕግ ክሱን ያሻሽላል፤ አሻሽሎ ላቀረበው ክስ ማስረጃውን ያቀርባል፡፡ፍ/ቤቱ ግን ስለ መከላከያ ማስረጃ ምንም (ይከላከሉ ወይም መከላከያ ማቅረብ አያስፈልጋቸውም) ሳይል ቀጥታ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔ ወደ መስጠት የሄደበት ምክንያት ምናልባት ድሮውንም ቢሆን መከላከያ ማስረጃ የለንም ብለው ስለነበር አሁንም አይኖራቸውም ከሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም ተከሳሾች መጀመሪያ መከላከያ ማስረጃ የለንም ስላሉ ብቻ ተሻሽሎ ለቀረበባቸው ክስ መከላከያ የሚሆን ማስረጃ ይኑራቸው አይኑራቸው ፍ/ቤቱ ሳያረጋግጥ ማለፉ አግባብ አልነበረም፡፡

- ዐ/ህግ ክሱን እንዲያሻሽል ታዞ ክሴ ምንም ስህተት የለበትም በማለት እንቢተኛ ከሆነ ምን መሆን አለበት? የሚለው ጥያቄ በለተያየ መንገድ አስተያየት ይሰጥበታል፡፡(1) በዐ/ህግ ላይ ትዕዛዝ ባለማክበሩ የሚወሰደው እርምጃ ካለ እንደተጠበቀ ሁኖ ፍርድ ቤቱ ባለው ክስ መሰረት አስቀጥሎ የመጨረሻ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል (2) ክሱ ተሻሽሎ እንኪቀርብ ድረስ መዝገቡን መዝጋት፤ተከሳሽ ታስሮ ከሆነ መልቀቅ የሚሉ ክርክሮች ይቀርባሉ፡፡የተሻለው የትኛው ነው?

2.4.2 **ክስን ስለ ማንሳት**

ክስን ማንሳት ሲባል በመሰማት ሂደት የነበረ ክስ በተለያዩ ምክንያቶች ሂደቱ እንዲቋረጥና መዝገቡ ለዘለቄታው ወይም ለጊዜው እንዲዘጋ የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ክስ የሚነሳበት ምክንያት /ሁኔታ/ በወ/መ /ስ/ስ /ሕጋችን በዓንቀፅ 122 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ቁ.(1) እንደሚያመለክተው በድሮው የወ/መ/ ሕግ ቁ.522 (በአሁኑ የወ/ሕግ ዓንቀፅ 539) ወይም በድሮው የወ/መ/ሕግ ቁ.637 (በአሁኑ የወ/ሕግ ዓንቀፅ 671) መሰረት ከቀረበው ክስ በስተቀር ዓ/ሕጉ በተከሳሹ ላይ ያቀረበውን ማንኛውም ክስ በፍርድ ቤቱ ፊቃድ ከፍርድ በፊት ክሱ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ክሱን ለማንሳት እንደሚችል ነው፡፡

- ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ በፍትህ ሚኒስቴር ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ እና ክልል ፍትህ ቢሮዎች ስልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ በዝምታ የተሸረ መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡
- ምክንያቱም ዐ/ህግ በማንኛውም ጊዜ በማንኛወም ወንጀል ክስ ማንሳት የሚችል መሆኑ በአዋጆቹ ተመልክቷል፡፡ለምሳሌ የአብክመ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 176/2005 አንቀፅ 22(10) ስር ዐ/ህግ ክስ ማንሳት የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት የፍርድ ቤት ይሁንታ ሳይጠብቅ ማንሳት የሚችል መሆኑ ነው፡፡

ክስ ማንሳት ጋር በተያያዘ የሌሎች የሕግ ስርዓቶች ተሞክሮ ስናይ፤

- የኮመንሎው የሕግ ስርዓት በሚከተሉ አገሮች ዓ/ሕግ በቂ ምክንያት ይኑሮው አይኑሮው በፈለገው ጊዜ ክሱን ማንሳት ይችላል፡፡
- በሲቭል ሎ የሕግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ግን ዓ/ሕግ ክስ ካቀረበ በኋላ የማንሳት ስልጣን (መብት)
- ከዚህ ጋር ተያይዞ ዐ/ህግ በማንኛውም ጊዜ ክስ ሊያነሳ የሚችል መሆኑ እና በዚያው ጉዳይ ክሱን ሊያስቀጥል የሚችል መሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 7 በመ/ቁ. 28952 ላይ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡
- ሌላው ክስ የሚነሳበት ጊዜ መቼ እንደሆነ ቁ.122 (1) ኣመልክቷል፡፡ ይኸውም ክሱን ማንሳት የሚቻለው ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ ነው ይላል፡፡ ከፍርድ በፊት ማለት ግራና ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃቸውን አቅርበው ካጠናቀቁ በኋላና መዝገቡ ለውሳኔ ከተቀጠረ በኋላ የክስ ማንሳት ጥያቄ የቀረበ እንደሆነም ተቀባይነት አለው ማለት ነው፡፡

- ለምሳሌ፡- ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃው አቅርቦ የዓ/ሕግ ማስረጃ ካስተባበለ በኋላ ክስ እንዳነሳ ይፈቀድልኝ ብሎ ለሚያቀርበው ጥያቄ ክስ እንዲሻሻል መፍቀድ ለተከሳሹን የሚጎዳ አይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡
- በሌላ በኩል ደግሞ ዓ/ሕግ ለጊዜው ብቃት ያለው ማስረጃ ባለማግኘቱ ክሱን በተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ የተስተባበለበት ቢሆንም ለወደፊቱ በበቂ ሁኔታ ሊያስረዳልኝ የሚችል ማስረጃ ላገኝ እችላለሁ ብሎ ሲያምን ክሱን እንዲያነሳ ቢፈቀድለት ወንጀለኞች እንዳያመልጡ ያግዛል የሚል አቋም ያቸው አሉ፡፡
- እንደ እኔ እምነት ከሆነ ግን ሁለተኛው አማራጭ መውሰዱ የፓሊስና የዓ/ሕግ ስንፍና የሚያባብስና ከጅምሩ በሚገባ ሁኔታ የተጠናቀረና ብቃት ያለው ማስረጃ አዘጋጅቶው እንዳይቀርቡ በር ከመክፈቱ በላይ ለተከሳሾች የሚጎዳና ጥፋተኛ ሊያደርጋቸው የሚችል ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ወይም በመከላከያቸው አስተባብለውት እያለ ክስ እንዲነሳ በመፈቀዱ ምክንያት ተንጠልጥሎ እንዲቀር የሚያደርግ ነው፡፡
- ከዚህ ጋር ተያይዞ ዐ/ህግ ጉዳዩ የሚያንቀሳቅሰው በዚያው መዝገብ ነው ወይስ በአዲስ ክስ? ልዩነት ስላለው ነው፡፡አዲስ ክስ ከሆነ ዐ/ህግ አዲስ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚያደርግ በመሆኑ በፍርዱ ላይ ለውጥ ያመጣል፤የቀድሞው መዝገብ የሚያንቀሳቅስ ከሆነ ግን ለውጥ ላያመጣ ስለሚችል ነው፡፡

2.5 የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያና በፍ/ቤቱ የሚሰጥ ትእዛዝ

2.5.1 የመጀመርያ መቃወሚያ (Preliminary objection)

ተከሳሹ ማንነቱ ካረጋገጠ በኋላ ፍ/ቤቱ ክሱን ለተከሳሹ ያነብለታል፡፡ ክሱ ግልፅ ስለመሆኑም ይጠይቀዋል፡፡ ተከሳሹ ክሱ ግልፅ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የመጀመሪያ መቃወሚያ ካለው ፍርድ ቤቱ ይጠይቃዋል፡፡ የመጀመርያ መቃወሚያ ያለው መሆኑን አለመሆኑን ሳያረጋግጥ ፍ/ቤቱ የእምነት ክህደት ቃል ወደ መቀበል መሄድ የለበትም፡፡

በተከሳሹ ሊቀርብ የሚችል መቃወሚያ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል፡፡ አንደኛ በቁ.130 (1) እንደተመለከተው ተከሳሹ **በክሱ ማመልከቻ ፎርም** ወይም ይዘት ላይ መቃወሚያ ሲኖሮው የሚቀርብ ነው፡፡ይህ ዓይነቱ መቃወሚያ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.111 እና 112 የተዘረዘሩትን ነገሮች የሚመለከት ነው፡፡

(1) በቁ. 111 ላይ የተመለከቱት ነገሮች ስናይ፤ ማንኛውም የክስ ማመልከቻ፡-

- ቀንና ዓመተ ምህረት የተፃፈበትና የተፈረመበት ፣

- የተከሳሹ ስም የያዘ ፣
- ተከሳሹ የተከሰሰበት እና የወንጀሉ መሰረታዊ ነገር ያካተተ ፣
- ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜና ስፍራ ያመላከተ ፣
- የተበደለው ሰው ስም ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት (ተገቢ በሆነ ጊዜ) የሚያመለክት፣
- ተከሳሹ ወንጀሉን በመፈፀም ተላልፏል የተባለበት የሕግ ዓንቀፅ የያዘ መሆነ አለበት፡፡

(3) በቁ.112 የተመለከተው ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል ለይቶ አውቆ መልስ ለመስጠት እንዲችል እያንዳንዱ ክስ ወንጀሉንና ሆኔታውን በዝርዝር መግለፅ እንዳለበት ነው፡፡ ስለዚህ በቁ.111 ወይም 112 ላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች (ነገሮች) አንዳንዶቹ በክሱ ማመልከቻ ላይ ያልተካተቱ ሆኖው ያገኛቸው እንደሆነ ተከሳሹ በመቃወሚያ መልክ ሊያነሳቸው እንዲሚችል ነው፡

በቁጥር 130(2) ከፊደል ተራ ቁጥር(ሀ እስከ ሰ) ስር የተመለከቱት መቃወሚያዎች ደግሞ ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ይሁን እንጂ በአጠቃላይ በቁ.130 የተጠቀሱት መቃወሚያዎች ሁሉን ያጠቃለሉ ናቸውን? አይደሉም፡፡አመላካች ናቸው፡፡ (የፌዴራል ሰ/ሰሚ ችሎት በቅጽ 14 በመ/ቁ. 73514)

- መቃወሚያዎቹ መቼ ይቀርባሉ? ክሱ በሚሰማበት ጊዜ ወዲያውኑ፤ በልዩ ሁኔታ ፍትህ የሚጓደል በሆነ ጊዜ ከፍርድ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሊነሳ የሚችል መሆኑ ተመልክቷል፡፡(ቁ.130 (3))
- ፍርድ ቤቱ በራሱ ጊዜ ሊያነሳቸው የሚችላቸው መቃወሚያዎች አሉን? የትኞቹ ናቸው? ይርጋ፣ሃላፊት፣ድጋሚ አለመከሰስን የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- የሚቀርበው በቃል ነው ሊጓተት አይገባም፡፡ክሱን የሚቃወም እንደሆነ ይጠይቀዋል ይላል...ቁጥር 129.

ተከታዮቹ መቃወሚያዎቹ ዘግይተው ቢቀርቡ እና ፍርድ ቤቱም በራሱ አነሳሽነት ቢቀርቡ ፍትሃዊ ነው፡፡

1) ቁ.130 (2) (ለ) ተከሳሹ በዚሁ ክስ ከዚህ ቀደም ተከሶ ነፃ የወጣ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ ወይም
2) ቁ.130 (2) (ሐ) ክስ የቀረበበት ወንጀል በይርጋ ሕግ የታገደ ወይም ምሕረት ወይም የኣዋጅ ምሕረት (ይቅርታ) የተደረገለት መሆኑን ወይም

3) ቁ.130 (2) (ሰ) ለፈፀማቸው ተግባሮች ሃላፊ ያለመሆኑን ባመለከተ ጊዜ ነው፡፡

(እንዚህ መቃወሚያዎች ተከሳሽን በእጅጉ የሚጎዱ ተግባራት ናቸው)

- የሚፀና ፍርድ ከመስጠት የሚያግድ መቃወሚያ ሲገኝ ዘግይቶም ቢሆን ሊነሳ ይችላል ብሎ ሕጉ ሲያስቀምጥ ይህን ተከትሎ የሚነሳ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ሳይነሳ ቀርቶ በይግባኝ ፍርድ ቤት ይግባኙ በሚታይበት ጊዜ ቢነሳስ ተቀባይነት አለው ወይ የሚል ይሆናል፡፡
- እንግዲህ ይህ ልዩ ሁኔታ ከአጠቃላይ የሕገ መንግስቱ መርሆዎችና ከቅጣት ዓላማ አንፃር መታየት ስላለበት በይግባኝ ፍርድ ቤት በሚሰማበት ወቅት የተነሳ መቃወሚያ ቢሆንም እንኳ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል፡፡
- በ1967 ዓ.ም በተወሰነ አንድ ጉዳይ አንድ ሰው የግድያ ወንጀል ፈፅሟል በሚል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ በ25 ዓመት ፅኑ እስራት ይፈረድበታል፡፡ፍርዱን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን የጠ/ፍ/ቤት ወንጀል ችሎትም መዝገቡ ከመረመረ በኋላ ክሱ በይርጋ ጊዜ የታገደ ሆኖ ስላገኘው በዞኑ ፍ/ቤት የተሰጠን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ውድቅ በማድረግ ይግባኝ ባይን በነፃ እንዲለቀቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

መቃወሚያ የተለየ ፎርም አለውን

- ከፎርም ጋር በተያያዘ በቁ.130 (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርበው መቃወሚያም ሆነ ዓቃቤ ሕጉ ለመቃወሚያው የሚሰጠው መልስ ሁሉ በቃል መቅረብ እንዳለበት ከቁ.131 (1) መረዳት ይቻላል፡፡ ተደጋጋሚ ስልጠናዎች እየተሰጡ አሁን አሁን እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በተግባር ሲሰራበት የነበረና አሁንም ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ብሎ በአስተማማኝ መናገር የማይቻለው፤
- ምክንያቱም በተግባር መቃወሚያ ለማቅረብ ጊዜ መስጠት ፣ መቃወሚያው በፅሑፍ ማቅረብ ፣ ዓ/ሕግ የመቃወሚያው ግልባጭ እንዲደርሰው ማድረግ ፣ ዓ/ሕግ በሚሰጠው ቀነ ቀጠሮ መልሱ በፅሑፍ ያቀርባል ፣ ተከሳሹ በበኩሉ የመልስ መልስ በፅሑፍ ለማቅረብ ጊዜ ይሰጠዋል ፣ በመጨረሻ ፍ/ቤቱ የተከሳሽ መቃወሚያና የዓ/ሕግ መልስ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ ይሰጣል፤ ምናልባት ምርመራው ያላለቀ ከሆነ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤቱ ብይን ይሰጣል፡፡ ይህ የተንዛዛ አካሄድ ሕጉ ከሚያዘው ውጭ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

2.5.2 መቃወሚያውን ስለመመርመርና ስለመወሰን

በቁ. 130 (2) መሰረት የሚቀርበውን ማንኛውንም መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ከፃፊ በኃላ ዓ/ሕጉ መልስ እንዳለው ይጠይቃል፡፡ የቀረበውን መቃወሚያ ሕግን በመጥቀስ ለመወሰን የሚቻል ከሆነ ወይም ዓ/ሕጉ መቃወሚያውን ካልተቃወመ ፍ/ቤቱ ወድያው ይወስናል (ቁ. 131 (1))፡፡ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማጣራት ማስረጃ መቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘውና ማስረጃ ሳይቀርብ ወድያው ውሳኔ (ብይን) መስጠት የማይቻል በሆነ ጊዜ አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (ቁ. 131 (3))፡፡የተፈለገው ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ ፍ/ቤቱ ወዲያው ውሳኔ መስጠት እንዳለበት ቁጥር 131 (4) ይደነግጋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ /ብይን/ እንደየ መቃወሚያው ዓይነት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸዉም፡-

ሀ) የቀረበው መቃወሚያ የሕግ ድጋፍ የሌለው ከሆነ ወይም በማስረጃ ካልተደገፈ መቃወሚያውን ውድቅ ያደርጋል ፣

ለ) በቁ. 130/ 2/ለ/፣ /ሐ/፣ ወይም/ሰ/ መሰረት የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ካገኘ ክሱን ዘግቶ ተከሳሹን ያሰናብታል ፣

ሐ) በቁ.130/2/ሀ/ መሰረት የቀረበ መቃወሚያ ከሆነ ጉዳዩ በተጀመረበት ፍ/ቤት እንዲቀጥል በማዘዝ መዝገቡን ይዘጋል ፣

መ) በቁ. 130(2) (መ) መሰረት የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ካገኘ ክሱ ተነጥሎ እንዲታይ ያዝዛል ፣

ሠ) በቁ. 130 /2/ሠ/ የቀረበ መቃወሚያ ከሆነ አስፈላጊው ፈቃድ እስኪሰጥ መዝገቡን ለጊዜው ይዘጋዋል ፣

ረ) በቁ. 130/2/ረ/ የቀረበ ከሆነ ደግሞ አስቀድሞ መፈፀም ያለበት ስርዓት እስኪፈፀም መዝገቡን ለጊዜው ይዘጋዋል፡፡

ከዚህ በላይ በፊደል “ለ” የተጠቀሰውን እንዳለ ሆኖ ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ ሃላፊ ባለመሆኑ ክሱ በተዘጋ ጊዜ የተከሳሹ ሁኔታ በፀጥታ ወይም በህዝብ ሰላማዊ ኑሮ ላይ ሁከት ወይም አደጋ የሚያደርስ መስሎ ከታየው ተከሳሹ ተገቢ በሆነ ስፍራ ወይም ሕክምና በሚያገኝበት ቦታ ተወስኖ እንዲቀመጥ ፍ/ቤቱ ያዝዛል (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 208 እና የወ/ሕግ ዓንቀፅ 130 እስከ 132) ፡፡

2.6 የእምነት ክሕደት ቃል ስለመስጠት /Plea of the accused)

ክሱን እየሰማ ያለ ፍርድ ቤት ተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ማዘዝ የሚችለው የመጀመሪያ መቃወሚያ ያልቀረበ እንደሆነ ወይም መቃወሚያው ቀርቦ የሕግ መሰረት የለውም ተብሎ ውድቅ ከተደረገ ወይም ሕጉ በሚያዘው መሰረት መዝገቡ ለጊዜው ካልተዘጋ ብቻ ነው። የእምነት ክሕደት ቃል (plea) ስንል ተከሳሹ ጉዳዩን በያዘው (ክሱን እየሰማ ባለው) ፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ ስለቀረበበት ክስ ፍሬ ነገር መፈፀሙን አለመፈፀሙን እና ጥፋተኛ መሆኑን አለመሆኑን ለመግለፅ የሚናገረው ቃል ማለት ነው።

2.6.1 ስለ እምነት ቃል (Plea of guilty)

በአጠቃላይ ስለ እምነት ቃል ሲወሳ ሁለት ነገሮች ወደ አእምሯችን ይመጣሉ፡፡እነሱም (1) ዐ/ሕግ እና ተከሳሽ በሚያደርጉት ስምምነት (Plea bargaining) በተከሳሹ የሚሰጥ እምነት ቃል አንዱ ሲሆን፣ (2) ሌላው ደግሞ ተከሳሹ ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ ክሱን ከተነበበለት በኋላ የሚሰጠው የእምነት ቃል (Plea of guilty) ነው።

- (1) የእምነት ቃል ለመስጠት **መስማማትን** /plea bargaining/ በዋነኝነት **በኮመን ሎው የሕግ** ስርዓት ተከታይ አገሮች የሚታወቅ ሆኖ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የሚያደርጉት ስምምነት ሲሆን ይዘቱም ተከሳሽ የእምነት ቃል እንዲሰጥና በአንፃሩ ደግሞ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ የሚያቀርበው ክስ እንዲቀንስ ወይም ተመስርቶ የነበረ ክስ ቀንሶ እንዲያነሳ ወይም ቅጣት እንዲቀልለት ለፍርድ ቤት ሓሳብ ማቅረብ ነው (አንዳንድ ጊዜ **እስከ 30% ቅጣት ይቀነሳል**) በእነዚህ አገሮች አብዛኛዎቹ የወንጀል ጉዳዮች ውሳኔ የሚያገኙት በእምነት ቃል መሰረት ነው። ለዚህ አሰራር መምጣት ምክንያት የሆኑት ደግሞ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የፍ/ቤት ጉዳዮች ለማቃለልና የክርክር ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበ በመምጣቱ ነው ይባላል።ይህ ስርዓት አሁን ባለው የስነ-ስርዓት ህግ ያልተካተተ በመሆኑ እየተተገበረበት አይደለም፡፡ምናልባል አሁን በረቂቅ ደረጃ ያለው ወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ይህን ስርዓት ያካተተው በመሆኑ ወደ ፊት ቢፀድቅ በፍትህ ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል የሚል ግምት አለ፡፡
- (2) ሌላው በፍትህ ተቋማት የሚደረግ የእምነት ቃል ነው፡፡ይህም ጉዳዩን በያዘው ችሎት ፊት የሚሰጥ የእምነት ቃል እና ከፍርድ ቤት ውጭ የሚሰጥ የእምነት ቃል ብለን ልንከፍለው እንችላለን፡፡

- ከመደበኛው የክርክር ሂደት ውጭ የተሰጠ የእምነት ቃል ማስረጃ የሚያስፈልገው እንጂ በእምነት ቃል መሰረት ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም። ለምሳሌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.35 እና 27 መሰረት የተሰጡ የእምነት ቃሎች በማስረጃ ሊደገፉ ይገባል።
- ተከሳሽ ክሱን በሚሰማው ፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ የሚሰጠው የእምነት ቃል ተቀባይነት በሚመለከት የተለያዩ የሕግ ስርዓቶች የተለያየ አቋም አላቸው።
- **የኮመን ሎው የሕግ ስርዓት** የሚከተሉ አገሮች ያየን እንደሆነ በተከሽ የሚሰጥ የእምነት ቃል በማንኛውም ሁኔታ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል ይላሉ። ስለሆነም አብዛኛው የወንጀል ጉዳዮች ውሳኔ የሚያገኙት ተከሳሾች በሚሰጡት የእምነት ቃል ነው ። ይሁን እንጂ ችሎቱ የእምነት ቃሉ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት ተከሳሽ ጠበቃ የታገዘ መሆኑ አለመሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።
- **በሲቪል ሎ የሕግ ስርዓት የሚከተሉ አገሮች** ግን ተከሳሹ በሰጠው እምነት ቃል መሰረት ብቻ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ በጣም ውሱን ነው።ስለሆነም በአብዛኛው ጊዜ ተከሳሽ የእምነት ቃል ቢሰጥም ማስረጃ የግድ መስማት አስፈላጊ ተደርጎ ይወሰዳል።
- የአገራችን የሕግ ስርዓት ስንመለከት ደግሞ መጀመሪያ የተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል ከመጠየቁ በፊት ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ በሚገባ እንዲረዳው ፍ/ቤቱ የክሱን ዝርዝር ለተከሳሹ ማስረዳት አለበት (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.132 (1) እና ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 20 (2) ይመለከቷል።)
- በመሆኑም ፍ/ቤቱ የወንጀሉን ዝርዝር፣ወንጀሉን የሚያቋቁሙ የሕግ ፣ የሞራል እና ግዙፋዊ ጠባዮች ሁሉ (Legal, material and moral elements of the offence) (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.111 (1) (ለ) እና የወ/ሕግ ዓነቀፅ 23) ፣ ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ሊወሰንበት የሚችለውን የቅጣት ዓይነትና የቅጣቱ መነሻና ጣሪያ ፣ የተከሳሹን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ማለትም ፣ ያለመናገር መብቱን ፣ ክሱን ለማመን ወይም ለመካድ ሙሉ መብት እንዳለው እና ጥፋተኛነቱን ማረጋገጥ የዓ/ሕግ ግዴታ መሆኑንና ጥፋተኛነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት ያለው መሆኑን ነው ። አስፈላጊው ገለፃ ከተደረገለት በኋላ ተከሳሹ የቀረበለትን ክስ መፈፀሙንና ጥፋተኛ መሆኑን የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን ፍ/ቤቱ ይጠይቃል።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ተከሳሽ የእምነት ክህደት ቃል ከመስጠቱ በፊት በቂ ገለጻ ሊደረግለት ሲገባ በተግባር ግን ጉዳዩ ለማሳጠር ሲባል በቂ ገለጻ ሳይደረግለት የእምነት

ክህደት ቃል እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ይህ በመሆኑም በበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ምስክር ሳላሰማ ተፈረደብኝ በማለት ቅሬታ ሲያቀርብ ይስተዋላል፡፡

ተከሳሽ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል መፈፀሙን ያመነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የእምነት ቃሉን ወድያው መቀበል የለበትም ። ቃሉን ከመቀበሉ በፊት ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ ያመነ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ። አንድ ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ ሙሉ በሙሉ አምኗል የሚባለው መቼ ነው? የሚል ጥያቄ በዚህ አጋጣሚ ማንሳት ተገቢነት አለው ። ተከሳሹ ወንጀሉን ፈፅሜአለሁ ብሎ ማመኑ ብቻ ሙሉ በሙሉ ማመኑን አያረጋግጥም ። ሙሉ በሙሉ አምኗል የሚባለው የእምነት ቃሉን የሰጠው በነፃ ፈቃዱ (voluntarily) መሆኑ ሲረጋገጥና ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያመለክቱ መሰረታዊ እውነታዎች (Factual basis) መኖራቸው ሲረጋገጥ ነው።

ፍ/ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች ለማጣራት የሚከተሉትን ማጣሪያዎችና ገለፃዎች ማከናወን አለበት፣

ሀ) ተከሳሽ የወንጀሉን ዝርዝር በትክክል መረዳቱን ጠይቆ ማረጋገጥ ፣

ለ) የተከሳሹን የእምነት ቃል ፍ/ቤቱ ከተቀበለው ወድያው የጥፋተኛነት ውሳኔ እንደሚሰጥና ተከሳሹ የመከላከል መብት እንደማይኖረው ማስረዳት ፣

ሐ) ወንጀሉን መፈፀሙን እንዲያምን ተፅእኖ ወይም ማስፈራራት ደርሶበት እንደሆነ ይህንኑ ከተከሳሹ ጠይቆ ማረጋገጥ ፣

መ) ተፅዕኖ ደርሶበት እንደሆነ ያለ ፈቃዱ እንዲያምን መገደድ እንደሌለበት ማስረዳት፣

ሠ) በክስ ማመልከቻው ላይ የተዘረዘረውን የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር ተከሳሹ ፈፀምኩ ከሚለው አገላለፅ (አነጋገር) ጋር በማስተያየት እንዲሁም ተከሳሹ ቢክድ ኖሮ ዓ/ሕግ ሊያቀርብ ያዘጋጀውን ማስረጃ በአጭሩ በመጠየቅ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያሳዩ መሰረታዊ እውነታዎች (Factual basis) መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት ።

ይህን ሁሉ ማጣሪያ ካደረገ በኃላ ፍ/ቤቱ ሁለት አማራጮች ይኖሩታል፡፡ ይኸውም

- በተከሳሹ እምነት ቃል ላይ ጥርጣሬ ካደረበት ዓ/ሕግ ማስረጃውን አቅርቦ እንዲያሰማ ለማዘዝና ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ ይችላል (ቁ.134 (2)) ።

- ተከሳሹ ወንጀሉን መፈጸሙ አኗል ብሎ የገመተ እንደሆነ ጥፋተኛ ነኝ ብሏል በማለት ከመዘገበ በኃላ በተከሳሹ ላይ ተጥፋተኝነት ውሳኔ ይሰጣል (ቁ.134/1/)።። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሲነሳ የሚገባው ነጥብ የስነ ስርዓት ሕጉ በተከሳሹ እምነት ቃል ብቻ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉና የእምነት ቃል ቢኖርም ከወንጀሉ ከባድነት አንፃር ታይቶ ማስረጃ ሊሰማባቸው የሚገባ የወንጀል ዓይነቶች ለይቶ አለማስቀመጡ ነው ።
- በልምድ እንደሚሰራበት ግን በዕድሜ ልክ ወይም በሞት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ ቢያምንም ፍ/ቤቱ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚያዝበት ሁኔታ ነው ያለው።

የፍትሕና ሕግ ስርዓት ምርምር ኢንስቲቱት ባዘጋጀው የወ/መ/ሥ/ሥሕ/ህግ ረቂቅ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ በዓንቀፅ 128 ላይ እንደተመለከተው ከሆነ ግን በተከላሹ እምነት ቃል ብቻ ሊወሰኑ የማይችሉና የሚችሉ ለይቶ አስቀምጧል ። የዓንቀፁ ይዘት እንደሚከተለው ይላል፤....(ተከሳሹ ጥፋተኛ ነኝ በማለት የእምነት ቃሉን ቢሰጥም ፍ/ቤቱ ማስረጃ ሰምቶ መወሰን አለበት ። ሆኖም የክስ አቤቱታ በማቅረብ በሚያስቀጣ በማንኛውም ወንጀል ወይም በደንብ መተላለፍ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ሳይሰማ በተከሳሹ የእምነት ቃል ብቻ የጥፋተኛነት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል) ይላል።

ይህ ረቂቅ እንዳለ ወይም በተወሰነ መልኩ በማሻሻል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያፀደቀው እንደሆነ ካለማወቃቸውና የባለሙያ ድጋፍ ሳያገኙ ወይም በሌላ ምክንያት፤ ያልፈፀሙትን ወንጀል ፈፅመናል ብለው ለሚያምኑ ተከሳሾች ጠቃሚና በሚያስተማምን ማስረጃ ተንተርሶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

(በእምነት መሰረት ጥፋተኛ ለማለት በወንጀል አይነት መከፋፈል ተገቢ ነውን? አቤቱታ በማቅረብ ለሚያስቀጣ ወንጀል በእምነት መሰረት ጥፋተኛ ማለት፤ከዚህ ውጭ ያሉት ወንጀሎች ደግሞ ቢያምንም ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ ጥፋተኛ ማለት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም። ተከሳሽ ማመኑ በዝርዝር ከገለጸ ምስክር መስማት ለምን አስፈለገ፤የሰው ሃይልና የፍርድ ቤቱ ጊዜ አለአግባብ ማባከን አይደለምን---ውይይት ያስፈልገዋል።

ይሁን እንጂ በተግባር በተደጋጋሚ እንደሚታየው ተከሳሹ የተከሰስኩበት ወንጀል ፈፅሜዋለሁ፣ ጥፋተኛ ነኝ በማለት የእምነት ቃሉን ከሰጠ ወንጀሉን ለምንና እንዴት እንደፈፀመው በዝርዝር ሳይገልፅ የጥፋተኝት ውሳኔ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡

- የአብክመ ሰ/ሰሚ ችሎት በ/መ/ቁ.41203 የእምነት ቃልን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ቢታይ መልካም ነው፡፡

2.6.2 ስለ እምነት ቃል መሻር (withdrawal of plea of guilty)

የእምነት ቃል አንዴ ከተሰጠ በኃላ ሊሻሻል ወይም ሊሻር የሚቻል ስልመሆኑ ሌላ መዳሰስ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የእኛ ሕግ ስለ ክስ ማሻሻል ወይም መሻር የያዘው አቋም ከማየታችን በፊት ሌሎች የሕግ ስርዓቶች የሚከተሉት መንገድ በአጭሩም ቢሆን መቃኘቱ ጠቃሚ ነው፡፡

የኮመን ሎው የሕግ ስርዓት ብንመለከት በተለይ የአሜሪካን አገር በምሳሌነት ብንወስድ የእምነት ቃል መሻር የሚቻልበትና የማይቻልበት ሁኔታ እንዳለ ነው ። ስለዚህ የእምነት ቃል ለመሻር በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የእምነት ቃል ለመሻር ከሚያስችሉ ሁኔታዎች ዋናዋዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡

1) አንድ ተከሳሽ ቀደም ሲል የሰጠሁት የእምነት ቃል ይሻርልኝ ማለት የሚችለው ጥያቄው በወቅቱ ያቀረበው እንደሆነ ነው ፡፡ ይህ አባባል ግን ፍርድና ቅጣት ከተሰጠ በኃላም ጥያቄው ሊቀርብ እንደሚችል ነው።
2) ፍትሓዊ ያልሆነ ነገር ለማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ግን ተከሳሹ የሚከተሉትን ነገሮች በማስረጃ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

ሀ) ጠበቃ ሳይኖሮው /ሳይመደብለት/ የሰጠው የእምነት ቃል ከሆነ፤

ለ) የእምነት ቃል የተባለው በተከሳሽ በራሱ ወይም በወኪሉ ያልተሰጠ ከሆነ ወይም ባላመነው ጉዳይ ጥፋተኛ ተደርጎ ከሆነ፤

ሐ) የተሰጠው የእምነት ቃል ከፈቃድ ውጭ ከሆነ ወይም የክሱ ዓይነትና የሚያስከትለው ቅጣት ካለማወቅ የተሰጠ ከሆነ፣

መ) ዓ/ሕግና ተከሳሽ በፕሊ ባርገይኒግ (plea-bargaining) በተሰማሙት መሰረት ተከሳሹ ተጠቃሚ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ የሚሉ ናቸው፡፡

የኮንቲኔንታል የሕግ ስርዓት ስናይ ግን በመሰረቱ በእነዚህ አገሮች የእምነት ቃል የሚባል ነገር ስለማይሰራና ስለማይቀበሉት ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ መፈፀሙን

ቢያምንም ፍርድ ቤቱ ማስረጃን መስማት ስለሚገደድ የእምነት ቃል መሻር የሚባል ነገርም አይኖርም ።

በእኛ አገር የሕግ ስርዓት የእምነት ቃል ማሻሻልን ያየን እንደሆነ የስነ ስርዓት ሕጉ ቁ.135 ስለዚህ ጉዳይ ደንግጎ ይገኛል ፡፡ በንኡስ ቁጥር (1) እንደተመለከተው "የተሰጠው ቃል የእምነት በሆነ ጊዜ እና ፍርድ ቤቱ ክሱን መስማት በሚቀጥልበት ጊዜ ጥፋተኛ አይደለሁም የማለት ቃል መመዝገብ የሚገባው ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም የሚለው ቃል ይመዘግባል ።" ይላል ።

ተሰጥቶ የነበረ እምነት ቃል እንዲሻሻል ሐሳቡ የሚያመነጨው ማን ነው? የሚል ጥያቄ መቼውም ቢሆን መነሳቱ አይቀርም ። ከሕጉ አነጋገር አንፃር ሲታይ ሐሳቡ የሚያመነጨው ፍርድ ቤት ብቻ ወይም ተከሳሽ ብቻ ነው ብሎ ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ (1) **ተከሳሽ ራሱ ሰጥቸው የነበረ የእምነት ቃል ተሸሮ ወይም ተሻሽሎ ጥፋተኛ እንዳልሆንኩ ይመዝገብልኝ** ሊል ይችላል፡፡ (2) **ፍርድ ቤትም ከተከሳሹ አነጋገርና ከሌላ ሁኔታ በመነሳት ጥፋተኛ ነው** ብሎ መዝግቦት የነበረ በመሰረዝ የክሕደት ቃሉን እንደሰጠ አድርጎ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል ብሎ ሊመዘግብለት ይችላል። የእምነት ቃል ማሻሻል ጥያቄ /ሐሳብ እንዲነሳ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ወይም ምክንያቶች በሕጉ የሰፈሩ አይደሉም ። ስለዚህ በዋነኛነት ለፍርድ ቤቱ የተተው ይመስላሉ ። የአሜሪካ በምሳሌነት ወስደን እንዳየነው ዓይነት የእምነት ቃል እንዲሻሻል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ሁኔታዎች በሕጉ ማስፈር የማይቻል ግን አልነበረም ።

ከእምነት ቃል ማሻሻል ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የመጨረሻ ነጥብ ፤ እምነት ቃልን የማሻሻል ጥያቄ መቼ መቅረብ (መነሳት) እንዳለበት ነው። በቁ.135(1) እንደተደነገገው የእምነት ቃል እንዲሻሻል ሐሳብ የሚቀርበው "... ፍርድ ቤቱ ክሱን መሰማት በሚቀጥልበት ጊዜ ..." እንደሆነ ነው ። **የቁ.135 ይዘት ስንመለከት** ፤ የንኡስ ቁ. (1) ብቻ ብናይ **"ፍ/ቤቱ ክሱን መሰማት በሚቀጥልበት ጊዜ"** የሚለውን ሐረግ የእምነት ክህደት ቃል ከተሰጠ እና የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሚደረግ የሚያመለክት ይመስላል። ይሁን እንጂ ቁ.135(2) "በተከሳሹ ላይ የተሰጠው **የጥፋተኝነት ውሳኔ ውድቅ** ይሆናል ።" ይላል። ስለዚህ በድምር ሲታይ የእምነት ክሕደት ቃል እንዲሻሻል ሐሳብ ማቅረብ የሚቻለው ወይም ፍርድ ቤቱ ማንሳት የሚችለው ተከሳሹ የእምነት ክሕደት ቃሉ

ካስመዘገበ ጀምሮ የጥፋተኝነት ውሳኔ እስከ ተሰጠበት ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን ከሕጉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል።

ተከሳሽም የእምነት ቃል አሻሽላለሁ ብሎ ለፍ/ቤቱ ሐሳብ ስላቀረበ እንደ መብት መቆጠር ያለበት አይመስልም ። ተከሳሹ የእምነት ቃል ሰጥቶ ፍርድ ቤቱም ቃሉን ተቀብሎ ከመዘገበ በኃላ ቃሉን ለመቀየር የወሰነበትን ምክንያት ለፍ/ቤቱ አስረድቶ ፍ/ቤቱም ካመነበት ተፈፃሚ መሆን የሚችል ነው።

2.6.3. ስለ ክህደት ቃል

አንድ ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ በሚመለከት ቃሉን እንዲሰጥ ጥያቄ ሲቀርብበት ያለው ሁለተኛ አማራጭ የክህደት ቃል መስጠት ነው ። ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ ክዷል የሚባለው ምን ዓይነት ቃል ሲሰጥ ነው የሚል ጥያቄ የሚመልስልን የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.133 ነው ። እንደ ቁ.133 (1) አነጋገር ተከሳሹ ለክሱ የክህደት ቃል ሰጥቷል የሚባለው፤

(1) **ለክሱ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ በሕገ መንግስት ዓንቀፅ 19 (2) መሰረት የተያዙ ሰዎች (ለተከሰሱ ሰዎችም ተፈፃሚነት አለው) ላለመናገር መብት ስላላቸው)**

(2) **ክሱን አልፈፀምኩትም ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ የካደ እንደሆነ፤ወይም**

(3) **በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.133 (2) እንደተመለከተው ተከሳሹ የወንጀል ድርጊቱን አምኖ ስለአፈፃፀሙ ምክንያት ያቀረበ እንደሆነ ፤ ጥፋተኛ አይደለሁም ብሏል ሲል ፍ/ቤ በመዝገብ መፃፍ እንዳለበት ነው ።**

በተግባር እንደሚታየው ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ የክህደት ቃሉ በሚሰጥበት ጊዜ (ቁ.133 (1)) በፍርድ ቤት በኩል የሚፈፀም ስህተት ባይኖርም ተከሳሽ በቁ.133(2) መሰረት ወንጀሉን መፈጸሙን አምኖ በአፈፃፀሙ ረገድ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ ከሆነ ቃሉን ሲሰጥ ግን አምኗል እየተባለ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ ይስተዋላል።

1.6.4 የክህደት ቃል ማሻሻል ተፈቅዷልን?

እዚህ ላይ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ተከሳሹ ቃሉን ለመቀየር ያነሳሳው ምክንያት ማቅረብ የሚገባው ሲሆን ፍ/ቤቱም ተከሳሹ ወንጀሉን መፈፀሙ እንዲያምን ተፅእኖ ወይም ማስፈራራት ደርሶበት እንዳይሆን፣ ጥፋተኛ ነው ካለ የመከላከል መብት እንደማይኖሮው፣ የወንጀሉን አፈፃፀም ዝርዝር ፈፅሞኩ ከሚለው ጋር የሚጣጣም መሆኑን፣ ወዘተ ካረጋገጠና ቃሉን የሚያስቀይር ሆኖ ካገኘው ቃሉን ተቀብሎ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠት የማይችልበት ሁኔታ ያለ አይመስልም ። ሆኖም የስነ ስርዓትሕጉ ቁ.135 (1) ተሰጥቶ የነበረ

የእምነት ቃል ጥፋተኛ አይደለሁም ወደሚል ቃል የሚቀየርበት እንጂ የክሕደት ቃል ወደ ጥፋተኛነት (እምነት) ቃል ሊቀየረ የሚችል ስለመሆኑ በአርእስቱ ከመጠቆም አልፎ የተከሳሹ የክህደት ቃል ስለማሻሻል የገለጸው ነገር ስለሌለ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት የሚከራከሩ አለ፡፡እናንተስ ምን ትላላችሁ፡፡

2.7 ስለ ማስረጃ አቀራረብ

2.7.1 አጠቃላይ

የማስረጃ አቀራረብ ጉዳይ ራሱ በቻለ በማስረጃ ህግ የሚካተት መሆኑ ይታወቃል፡፡ይሁን እና የክስ መሰማት ሂደት ሲነሳ ካለ ማስረጃ አቀራረብ የተሟላ ገፅታ ስለማይኖረው የተወሰኑ ነጥቦችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡አሁን ባለው የአገራችን የህግ ስርዓት ራሱን **በቻለ በተጠቃለለ መፅሐፍ መልክ (ኮድ) የዘጋጀ የማስረጃ ህግ የለም፡፡የማስረጃ ህጎቹ በስነስዓት እና በፍሬ ነገር ሕጎቻችን ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ ይታወቃል፡፡** አሁን ለያዝነው ርእሰ ጉዳይ አግባብነት ያለው በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚቀርብ ማስረጃ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ህግ ውስጥ የተመለከተውን ብቻ ዳሰሳስን እናልፋለን።

አንድ የወንጅል ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ለክሱ የእምነት ቃሉን የሰጠና ፍርድ ቤቱም ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘው ጊዜ ባመነው መሰረት እንደሚፈረድበት ከላይ ተመልክተናል (ቁ. 134(1)) ፡፡ ማስረጃ መቀበልና መስማት አስፈላጊ የሚሆነው ተከሳሹ ቢያምንም ፍ/ቤቱ ማስረጃ መስማት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘውና ተከሳሹ ለክሱ ሙሉ በሙሉ ወይም በአፈፃፀሙ የካደ አንደሆነ ነው (ቁ. 133) ቢሆንም ማስረጃ (ምስክሮች) እንዲቀርቡ የሚታዘዘው ተከሳሹ የእምነት ክሕደት ቃሉን ከሰጠ በኃላ ሳይሆን ክሱ እንደቀረበና ክሱን ለመስማት ቀነ ቀጠሮ እንደተያዘ ወድያው ነው። **በመሆኑም ክርክሩ በሚሰማበት የመጀመሪያ ቀን ዓ/ሕጉ እና ተከሳሹ ይጠቅሙናል (ያስረዱልናል) የሚሉዋቸውን ምስክሮች፣የሞያ ምስክሮች(ኤክስፐርቶች)፣ ኢግዚቢቶችና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ካሉዋቸውም አሟልተው ማቅረብ ይጠበቅባቸውል (ቁ.123 እና 124)፡፡**

2.7.2 ሊቀርብ የሚገባ የማይገባ ማስረጃ

- ጭብጡን ሊያስረዱ የሚችሉ ቀጥተኛ ማስረጃዎች

  እነዚህም የሰው ማስረጃዎች(ተራ ምስክሮች፣ የሞያ ምስክሮች፣ የደረጃ ምስክሮች) የሰነድ ማስረጃዎች፣ኢግዚቢቶች (ገላጭ) ማስረጃዎች የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- ቀጥተኛ ያልሆነ

የስሚ ስሚ ማስረጃም ሊቀረብ ይችላል (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.138(1))

- በቀዳሚ ምርመራ ጊዜ የተሰሙ የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል በሰነድ ማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ሁኖም የሚቀርበው ምስክሩ የሞተ፤የአእምሮ ጉድለት ያገኘው እንደሆነ፣ማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ፤ ወይም በህመም በይም ከአገር በመውጣቱ ምክንያት መቅረብ ያልቻለ እንደሆነ ነው (ቁጥር 144(1))
- የልዩ አዋቂ ምስክርነት ቃል ግን በምስርነት ባይጠራም በቀዳሚ ምርመራ ጊዜ የሰጠው ቃል በማስረጃነት ይቀርባል፡፡(ቁጥር 144(1)) ለምን?
- በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ የእምነት ቃል አስፈላጊ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ሊመለከተው ይችላል፡፡ሆኖም ይህ ከመሆኑ በፊት ተከሳሹ በዚሁ ሰነድ ላይ አስተያት ካለው ይቀረበለዋል፤፤ቁጥር 145
- በቀዳሚ ምርመራ ጊዜ ተከሳሽ የሰጠው የእምነት ቃል በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ቁጥር 35 መሰረት የተሰጠ
- የተከለከሉ ማስረጃዎች
    - በማስገደድ ተገኘ ማስረጃ (የኢፌዲሪ የወ/ህ/ቁ.19(5))
    - ህግን በመተላለፍ የተገኘ ማስረጃስ? ለምሳሌ ፖሊስ የመበርበሪያ ትዕዛዝ ሳይዝ ሌሊት ስድስት ሰዓት ላይ ከሰው ቤት ገብቶ በርብሮ የሚያገኘው ማስረጃ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባልን?
    - ቀድሞ የጥፋተኝነት ሪከርድ (የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.138(1))
    - ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው ማስረጃ
    - ተከሳሽ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.146 መሰረት አንድ ማስረጃ እንዳይቀርብ ተቃውሞ ፍርድ ቤቱ ተቃውሞው የተቀበለው እንደሆነ ማስረጃው ሊቀርብ አይገባም፡፡

2.7.3 ምስክሮች ተሚልተው ባልቀረቡ ጊዜ ስለሚፈፀም ስነ ስርዓት

ሀ) በመጀመሪያው ቀጠሮ

ቀጠሮ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.94 ስር የተጠቀሱ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ መሰረት ቀጠሮ ሊለወጥ የሚችል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ይሁን እንጂ በተለያየ ምክንያት የግራ ቀኙ ምስክሮች ሳይቀርቡ የሚቀሩበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ

ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ተገቢ የሆነውን ትዕዛዝ ሊሰጥ ይገባል፡፡ለምሳሌ፡-

በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ምን ይወሰናል፡-

- የዐ/ህግ ምስክሮች ተሟልተው ቀርበው የመከላከያ ምስክሮች ካልቀረቡ፤
- የዐ/ህግ ምስክሮች ተሟልተው ቀርበው የተወሰኑ የመከላከያ ምስክሮች ቢቀርቡ
- የተወሰኑ የዐ/ህግ ምስክሮች ቀርበው ምንም የመከላከያ ምስክሮች ካልቀቡ
- የተወሰኑ የዐ/ህግ ምስክሮች እና የተወሰኑ የመ/ምስክሮች የቀረቡ እንደሆነ
- የተወሰኑ የዐ/ህግ ምስክሮች ቀርበው የመከላከያ ምስክሮች ተሟልተው የቀረቡ እንደሆነ

ለ) <u>በሁለተኛው ቀጠሮ</u>

ከላይ በ (ሀ) ስር በዝርዝር እንደተገለፀው በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያልቀረቡ የዓ/ሕግና የተከሳሽ ምስክሮች እንዲቀርቡ ድጋሚ የሚታዘዘው ይቀርባሉ የሚል እምነት በመያዝ ነው፡፡ እንዲቀርቡ በታዘዙት ቀን ካልቀረቡ ግን የሚከተሉትን መፈፀም ያስፈልጋል፡፡

- **የዓ/ሕግ ምስክሮች ሆኑ የተከሳሹ መከላከያ ያልቀረቡት በዓ/ሕጉ ወይም በተከሳሹ ጥፋት ካልሆነ የመጀመሪያውን ቀጠሮ ያህል ወይም ከዛ ያነሰ አንድ ተጨማሪ ቀጠሮ ለሰጥ ይችላል፡፡** (ቁ.95 (2))
- ምስክሮቹ ያልቀረቡት በዓ/ሕጉ ወይም በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ ግን ሌላ ቀጠሮ መስጠት ተገቢ እንዳልሆነ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 95 (2) ስር ከተመለከተው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡
- በግራ ቀኙ ጥፋት ምክንያት ምስክሮች ባልቀረቡ ጊዜ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት አስፈላጊ ያልሆነበት ምክንያት ክሱ በአፋጣኝ መሰማትና ውሳኔ ማግኘት ስለ አለበት ነው፡፡ተከሳሹ የተለያየ ምክንያት(ዋስትና በመነፈጉ፤ዋስ በማጣቱ) በማረሚያ ቤት የሚገኝ ከሆነ ምስክሮች ባለመቅረባቸው ምክንያት ለበርካታ ጊዜያት ምናልባትም ሊቀጣ ከሚገባው በላይ ታስሮ ይቆያል፡፡በዚህ ሁኔታ ተከሳሹ ታስሮ እንዲቆይ የሚደረግበት ምክንያት ለተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት እንዲቀጣ ሳይሆን በቀን ቀጠሮው ፍ/ቤት እንዲቀርብና ተገቢውን ፍርድ በሕግ መሰረት እንዲያገኝ ለማረጋገጥ ነው፡፡ነገር ግን ይህ ዓይነቱ እስራት ወንጀል ላልሰራ ንፁሕ ሰው ከባድ የሂሊና ሕመም ይፈጥራል፡፡ጥፋተኛ መሆኑ ገና በፍርድ ሳይረጋገጥ ተከሳሹ እየተቀጣ በመሆኑ በወንጀል ተግባር የተከሰሰ ማንኛውም ሰው

በፍርድ ቤት ካልተወሰነበት በቀር እንደጥፋተኛ አይቆጠርም የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌም ይፃረራል። እንዲህ ዓይነቱን ጉዳት ለመቀነስና ተከሳሹ ረዘም ላለ ጊዜ እንዳይንገላታ ለማድረግ ክሱ ባአፋጣኝ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባዋል።

2.7.4 ምስክሮችን መስማት

2.7.4.1 የዐ/ሕግ ምስክር መስማት

ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ መልስ ካልሰጠ ወይም የተከሰሰበትን ድርጊት አልፈፀምኩም ብሎ በግልፅ የካደ እንደሆነ ወይም ደግሞ ወንጀሉን መፈፀሙን አምኖ አፈጻጸሙ በተመለከተ መብቱን ጠብቆ የተከራከረ እንደሆነ ወይም ቀደም ሲል የእምነት ቃል ሰጥቶ ከቆየ በኋላ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ የካደ ከሆነ ዓቃቤ ሕግ ላቀረበውን ክስ ያስረዱልኛል የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ በማሰማት ማስረዳት አለበት።

- ዐ/ህጉ ምስክሮቹን ከማሰማቱ በፊት ያቀረበውን ክስና የሚያቀርበውን ማስረጃ ዓይነት በአጭሩና ያለ አድልዎ በመግለፅ ክሱን መክፈት አለበት (ቁ.136 (1)። ዐ/ህጉ የሚገልፀው በተለምዶ ጭብጥ እየተባለ የሚጠራው በክሱ የተዘረዘሩ ፍሬ ነገሮች እነዚህን ፍሬ ነገሮች የሚያረጋግጥለት ማስረጃ የቱ መሆኑን የሚገልፅበት ነው። በዓ/ሕግ የቀረቡ ምስክሮች በክሱ ፍሬ ነገር ላይ ያላቸው እውቀት ሊለያይ ይችላል፤ የሰነድ ማስረጃ ካለውም ምስክሮች የማያውቁትን ፍሬ ነገር የሚያስረዳለት ሊሆን ይችላል፣ ሌላ የማስረጃ ዓይነት ካለም እንዲሁ። ይህ ሁኔታ ሲኖር ዓ/ሕጉ ማን ምን እንደሚያስረዳለት በሚገባ ዘርዝሮ ማስቀመጥ አለበት፤ ፍ/ቤቱም ይህን ሳያደርግ ማለፍ የለበትም።
- በልምድ እንደሚሰራበት ግን ዓ/ሕግ ስለጭብጡ ሓሳቡን እንዲያቀርብ (እንዲገልፅ) ሲጠየቅ ምስክሮቼ የሚያስረዱልኝ እንደ ክሱ ነው በማለት በጣም አጠቃላይ በሆነ መልኩ ሲያስቀምጥ ነው የሚታየው።ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው ምስክሮቹ በተፈፀመው ወንጀል ያላቸውን እውቀት የተለያየ ሊሆን ይችላል።(ማን ምን እንደሚመሰክር ከታወቀ የትኛው ምስክር ቀድሞ እንዲሰማ መለየት የሚቻል በመሆኑ በዚሁ መሰረት ቅደም ተከተሉ ጠብቆ ስማት ስለሚቻለ--ጊዜ ይቆጥባል)
- የዓ/ሕግ ማስረጃ የሰነድ በሚሆንበት ጊዜም የሚሰተዋል ችግር አለ።የሰነድ ማስረጃው ኣስቀድሞ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ እንደሚያያዝ ግልፅ ነው።ሆኖም ማስረጃ በሚሰማበት ቀን ዓ/ሕግ ስለሰነድ ማስረጃው ዋና ይዘትና ሊያስረዳው የሚችል ነገር

ምን እንደሆነ ለፍ/ቤቱ መግለፅ ሲገባው ይህን ሳያደርግ የሚቀርበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ይታይል፡፡ ፍ/ቤቱም ትኩረት ሳይሰጠው ይቀራል፡፡

- ምስክሮች የምስክርነት ቃለቸውን ከመስጠታቸው በፊት መማል ወይም እውነትን ለመናገር ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ይህ ስነ ስርዓት ተደረገ ለማለት ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ምስርክር የሚሰጠው የምስክርነት ቃል ተከሳሽን **ጥፋተኛ ወይም ነፃ የማስደረግ ውጤት** ስላለው ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡**የመሃላ ፎርሙና ይዘቱ** ደግሞ “**በዚህ ፍ/ቤት ፊት የምሰጠው ቃል እውነት ፣ በሙሉ እዉነት ፣ እውነት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይሆን እምላለሁ**” የሚል መሆን አለበት፡፡ምስክሩ “እምላለሁ” ማለትን ሃይማኖቱ የማይፈቅድለት ወይም ምናልባት ሃይማኖት የሌለው ከሆነ “እምላለሁ” በማለት ፋንታ “አረጋግጣለሁ” ካለ በቂ እንደሆነ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡ ልምዱ እንደሚያሳየን ምስክሩ ክርስትያን ከሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ይዞ ፣ እስላም ከሆነ ደግሞ ጣቱን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ እንደሚምል ነው፡፡ የስነ ስርዓት ሕጉ ግን ምስክሩ ምን ይዞ ወይም እንዴት መማል እንዳለበት ያለው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ **መፅሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን** ይዞ ወይም ጣቱን ወደ ላይ ከፍ አድርጎ እንዲምል ማስገደድ አስፈላጊ አይደለም፡፡

- በሌላ በኩል ግን እውነቱን አለመመስከር ወይም በሓሰት መመስከር በወንጀል ሕግ እንደሚያስጠይቅ እንዲያውቁት መንገር ተገቢነት ሳይኖሮው አይቀርም(የወንጀል ሕጋችን በዓንቀፅ 453 እንዳመለከተው)፡፡ስለዚህ እውነቱን ካልተናገረ የሚያስከትልበት ቅጣት ከባድ መሆኑን አውቆ እንዲመሰክር ሊነገረው ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡
- **ሌላ መፈፀም ያለበት ስነ ስርዓት፤ ፍ/ቤቱ የያንዳንዱን ምስክርነት ሲቀበል መጀመሪያ የምስክሩን ስም፣ አድራሻውን፣ ስራውንና ዕድሜውን እንዲሁም መሐላ ማድረጉን ወይም እውነት ለመናገር ማረጋገጡን መጥቀስ አለበት (ቁ.147 (1)) ፡፡ እንዲሁም ምስክሩ ከተከሳሹ ወይም ከተበዳዩ ጋር ያለው ዝምድና ወይም ቅርበት** ወይም ፀብ (ጥላቻ) መጠየቁ ጠቃሚ ነው፡፡ ጠቃሚ የሆነበት ምክንያትም በማስረጃ ምዘና ጊዜ ግምት ውስጥ ለማስገባት ስለሚረዳ ነው፡፡

- እያንዳንዱ ምስክር ማንነቱ ካረጋገጠ በኋላ መጀመሪያ ዐ/ህግ ሕጉ ዋና ጥያቄ (Examination in chief) ፣ ከዚያም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው መስቀለኛ ጥያቄ(Cross Examination) ፣ በመጨረሻም ዓ/ሕጉ ድጋሚ ጥያቄ (Re-examination) ይጠይቁዋቸዋል፡፡
- **ዋና ጥያቄ** የሚባለው ምስክሩን ያቀረበው ወገን በመጀመሪያ የሚያቀርበው ጥያቄ ሲሆን አላማውም ምስክሩን የጠራው ወገን በክርክሩ ያለውን አቋም እንዲደግፍለት ለማድረግ ሲሆን ምስክሩም በጭብጥ ስለተያዘው ፍሬ ነገር **በቀጥታም ሆነ ቀጥታ** ባልሆነ መንገድ የሚያውቀውን እንዲያስረዳ ለማድረግ ነው፡፡በዋና ጥያቄ ጊዜ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ካልፈቀደ ዓ/ሕጉ መሪ ጥያቄ መጠየቅ እንደማይችል ተደንግጓል (ቁ.137 (1)(2))፡፡ይሁን እንጂ በዋና ጥያቄ መሪ ጥያቄ እንዲጠየቅ የሚፈቀደው መቼ ነው? የሚለው ህጉ ምላሽ አይሰጥም፡፡
- **መስቀለኛ ጥያቄ** የሚባለው ምስክሩን ያቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ ጠይቆት እንዳበቃ ሌላኛው ወገን የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፡፡የመስቀለኛ ጥያቄ ዓላማ በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት ቃል፣ የሚያጠራጥር ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለፍ/ቤቱ ለመግለፅና ለማስተባበል ነው (ቁ.137 (3)) ፡፡ ስለሆነም በዋና ጥያቄ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወዲዚያ የማያመራ አዲስ ነገር በመስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ሆኖም በመሰቀለኛ ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- **ድጋሚ ጥያቄ** ምስክሩን ያቀረበው ወገን ምስክሩ መስቀለኛ ጥያቄ ተጠይቆ ከአበቃ በኃላ የራሱን ምስክር ለሁለተኛ ጊዜ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡የድጋሚ ጥያቄ ዓላማም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመስቀለኛ ጥያቄ ያነሳውን ነገር ለማጣራት ብቻ የሚቀርብ ጥያቄ ነው (ቁ.139) ፡፡ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ጊዜ ከተነሳው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም አዲስ ነገር በድጋሚ ጥያቄ ማንሳት አይቻልም፡፡

- **ማጣሪያ ጥያቄ** ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ጊዜ የመጠየቅ መብታ አለው፡፡

- **ሌላ በሕግ በግልፅ ካልተፈቀደ በቀር የተከሳሽ የጥፋተኝነት ታሪክ ከፍርድ በፊት መግለፅ በቁጥር 138 መሰረት የተከለከተ ስለሆነ** ይህን የሚያመለክቱ ጥያቄዎች

ለምስክሩ መቅረብ የለባቸውም፡፡የዚህ አመክንዮ ተከሳሹ በተያዘው ክስ ጥፋተኛ ሳይባል ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ስለተከሳሹ የጥፋተኝነት ሪኮርድ ያወቀ እነደሆነ ዳኞች በነፃ ሀሊናቸው ውሳኔ እንዳይሰጡ ሊያደርጋቸው ይችላል ከሚል ነው፡፡

- **ምስክሮች የሚቀርብላቸው ጥያቄ በነፃና በመሰላቸው መንገድ ሊመልሱት ይገባል፡፡ ዓ/ሕግ ያቀረበው ምስክር ክሱን በሚጎዳ ሁኔታ ቢመሰክር ዓ/ሕጉ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍ/ቤቱን መጠየቅ የለበትም፡፡ ጥያቄው ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት፡፡ ዓ/ሕጉ ጥያቄውን ቢያቆምም ፍ/ቤቱ ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን መመርመር መቀጠል ይችላል፡፡**

- የምስክሮች ቃል ሲመዘገብም ዋና ጥያቄ ፣ መስቀለኛ ጥያቄ ፣ እና ድጋሚ ጥያቄ ተብሎ መከፈልና እያንዳንዱ የጥያቄ ዓይነት የሚጀምርበትና የሚያልቅበት ቦታ በሚያሳይ መልኩ መመዝገብ አለበት፡፡የአመዘጋገቡ ስርዓትም በዋነኛነት በሓተታ መልክ መሆን አለበት፤ እያንዳንዱ ቃል በምስክሩ ኣገላለፅ መመዝገብ ይገባዋል (ቁ.147 (3) (4)) ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ተከሳሽ የዐ/ህግ ምስክሮችን የመስልኛ ጥያቄ የመጠየቅ ሃሰተኛነቱን የማረጋገጥ መሰረታዊ መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ይሁን እንጂ ተከሳሽ ምስክሩን መስማት በማይቻልበት ሁኔታ ችሎቱን ቢረብሽ ፍርድ ቤቱ ምን ማድረግ ይገባዋ? ምስክር የመስማት ሂደቱን ማቋረጥ ወይስ ተከሳሹን በችሎት መድፈር ከመቅጣት ባለፈ ተከሳሹን አስወጥቶ የመስክር መስማቱ ሂደት ማስቀጠል? ውይይት ያስፈልገዋል፡፡

የማስረጃ ምዘና ብይን

(ሀ) ማስረጃ ምዘና

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሶስት መለኪያዎች አሉ እነዚህም፡-

(1) Beyond reasonable doubt (በተለምዶ ከበቂ ጥርጣሬ በላይ የምንለው ነው፡፡በኮመን ሎ በተለይም በአሜሪካ ተቀባይነት ያገኘ ስታንደርድ ነው፡፡

(2) Clear and convincing standard ግልፅና አሳማኝ የምንለው ነው፡፡ይህ ማስረጃ ከበቂ ጥርጣሬ በታች ሁኖ ግልጽና አሳማኝ በሆነ መንገድ ማስረዳት ማለት ሲሆን ነው ከ Preponderanece (የተሻለ ማስረጃ ያቀረበ) ከሚለው ስታንዳርድ ያነሰ ነው ፡፡ ...በአውሮፓ ሃገራት ይዘወተራል፡፡

(3) Preponderanece የተሻለ ማስረጃ ያቀረበ ለፍትሃ ብሄር ክርክር ተቀባይነት ያለው ስታንደርድ ነው፡፡

- የእኛ የወንጀል ማስረጃ ምዘና በየትኛው ይመደባል የሚለው ለመወሰን አስቸጋሪ ቢሆንም ከሁለተኛው መለኪያ ጋር የሚመሳሰል ሁኖ ይታያል፡፡ ቁጥር 141 (**በቂ ሁኖ ያላገኘው እንደሆነ**) የሚለው ሃረግ ተከላከል ለማለት ማስረጃው አሳማኝ እና በቂ ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ይመስላል፡፡
- ይሁን እንጂ በህጉ ላይ ያልተመለከተውን የማስረጃ ምዘናው ***ከበቂ ጥርጣሬ በላይ*** የሚለው መለኪያ እንደሆነ ተደርጎ ሲጠቀስ ይስተዋላል፡፡

(ለ ብይን

(1) ዐ/ህግ ክሱን ባላስረዳ ጊዜ

- የዐ/ህግ ማስረጃ ተከሳሽ ወንጀሉን ስለመፈፀሙ በቂ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ካላረጋገጠ" ተከሳሽ በነጻ ይሰናበታል፡፡እንዲህ በመሆኑ ጊዜ በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ እልባል የሚሰጥ በመሆኑ መዝገቡ በጥንቃቄ ሊመረመር ይገባል፡፡
- ፍርድ ነውና የዐ/ህግ ማስረጃ ውድቅ የተደረገበት አግባብ በብይኑ ሊጠቀስ እና በግልፅ ሊተች የሚገባ ነው፡፡

(2) ዐ/ህግ ክሱን ባስረዳ ጊዜ

- ተከሳሽ መከላከል እንዲጀምር ይነግረዋል (ቁጥር 142(1)
- ተከላከል ተብሎ ብይን የሚሰጠው ተከሳሽ መከላከያ እንኳ ባይኖረው ጥፋተኛ ሊያስብለው የሚችል መሆን አለበት፡፡ይሁን እንጂ ጥርጣሬም እያለ በመከላከያ

ማስረጃ ይጣራ ተብሎ ብይን የሚሰጥበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሳይችል ሲቀር ቀድሞውኑ ግልፅና አሳማኝ ባልሆነ ማስረጃ ተከላከል የተባለ በመሆኑ ምክንያት ተከሳሽ ባልፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛ የሚባልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡

እንዲህ በሆነ ጊዜ ምን አይነት ትዕዛዝ ይሰጣል የሚለው አከራካሪ ነገር ነው፡፡

- አንዳንድ ዳኞች ህጉ **መከላከል ይጀምር የሚል** በመሆኑ ዝርዝር እና ረጅም ውሳኔ መፃፍ አይገባም፣ አያስፈልግምም የሚል ክርክር የሚያነሱ አሉ፡
- በአንፃሩም የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል በመመዘን በየትኛው ድንጋጌ እንደተመሰከረበት ሁሉ ተለይቶ፤በተመሰከረበት መጠን ድንጋጌው ተቀይሮ ተከላከል ሊባል ይገባል የሚሉ አሉ፡፡በቁጥር 113(2) ስር በግልፅ እንደተመለከተው ከተከሰሰበት ወንጀል ያነሰ ወንጀል መፈፀሙ በማስረጃ ከተረጋገጠ በዚሁ ድንጋጌ ተከላከል ይባላል፡፡

- **እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ተከሳሽ የተሰሰበት ድንጋጌ ቀይሮ ተከላከል ማለት ተገቢ መሆኑ እና አለመሆኑ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡**
- **ህጉ በግልፅ እንደሚያሳየው መከላከሉን ይጀምር የሚል እንደሆነ ያመለክታል፡፡**
- **ምናልባት ድንጋጌው ተቀይሮ ተከላከል ከተባለ የድንጋጌው መቀየር ውሳኔውን ለሚሰሩት ዳኞች ይገዛቸዋልን? ይሕ ማለት በተሰጠው ብይን ሳይወሰኑ የመጨረሻው ፍርድ መስጠት ይችላሉን? የሚል ነው፡፡**
- **በአንድ በኩል ልክ ዳኞች መዝገቡ ባለበት ሁኔታ እንደሚያስቀጥሉ ሁሉ የተሰጠው ብይንም ልክ እንደችሎት ስራ ተቆጥሮ ዳኞች የተሰጠው ብይን ሊያከብሩ ይገባል የሚል አቋም የሚያንፀባርቁ ዳኞች እንዳሉ ሁሉ ብይን ተከሳሽ እንዲከላከል እድል የሚሰጥ ከሚሆን ውጭ ሌላ ሊሆን አይገባም ብለው የሚከራከሩ እንዳሉ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡**
- በእርግጥ ድንጋጌ መቀየር ከዋስትና አንጻር ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ይሁን እንጂ ችሎት ለመወሰን በተሰየሙት ዳኞች ላይ ግን በነጻ ፈቃዳቸው እንዳይወስኑ የሚደርግ ተግባር ነው፡፡

- ከዚህም ባሻገር ፍርዱን የሚሰራው ችሎት ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልገው ነው ተከላከል የተባለው የሚል እምነት ከያዘ በብይኑ ሳይወሰን ተከሳሽን በነፃ ሊያሰናብተው ይችላልን? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡

2.7.4.2. **የመከላከያ ምስክሮችን መስማት**

- የተከሳሽ የመከላከል መብት ሕገ መንግስታዊ መሰረት ያገኘ በመሆኑ መሰረታዊ መብት ነው::በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 20(4) እንደተመለከተው የተከሰሱ ሰዎች"...ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ኣላቸው::..." ይላል:: ይህ መሰረታዊ መብት በስነ ስርዓት ሕጉም ቢሆን ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የስነ ስርዓት ሕጉ በሚያዘው መሰረት መብቱን መጠቀም ይችላል::

- በመሰረቱ የመከላከያ ምስክሮች የመስማት ስነ ስርዓት አፈፃፀም ከዓ/ሕጉ የምስክሮች አሰማም ስነ ስርዓት የተለየ ኣይደለም:: በዚህ መሰረት ተከሳሹ ወይም ጠበቃው በመከላከያ ሊያስረዳ ያቀረበውን ማስረጃ በአጭሩ በመግለፅ መከላከያው የማሰማት ሂደቱ ይከፍታል (ቁ.142(2)) ::እዚህ ላይ ተከሳሹ መግለፅ የሚጠበቅበት ነገር ያቀረባቸው ምስክሮች ወይም ሌላ ማስረጃ ምን እንደሚከላከሉለት እንዳየ እውቀታቸው (በጉዳዩ ላይ ያላቸውን እውቀት) ለያይቶ ማስመዝገብ ነው:: ምስክሮቹ በየተራ እየተጠሩ እንዲመሰክሩ የሚደረግ ሲሆን ከዛ በፊት ግን ስለ ዓ/ሕግ ምስክሮች የተገለፀውን የመሃላ ፎርምና ይዘት መሰረት ኣድርገው መማል አለባቸው::

- በመርህ ደረጃ ተከሳሹ ማሰማት የሚችለው ማስረጃ በቁ.124 መሰረት ባቀረበው ዝርዝር ላይ ያሉትን ምስክሮች ነው:: ሆኖም ግን በዓ/ሕግ ምስክር እንዳየነው በዝርዝሩ ላይ ያልተጠቀሰ ምስክር እንዲቀርብለት ተከሳሹ ከጠየቀና ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተቀበለው ምስክሩ እንዲቀርብለት ሊያዝዝ ይችላል (ቁ.143 (2) :: በተጨማሪም የነገሩ መሰማት ከተጀመረ በኋላ ክሱ የተሻሻለ ወይም አዲስ ክስ የተዘጋጀ ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ተከሳሹ ከተሰሙት ምስክሮች ውስጥ ማንኛውም እንደገና አስጠርቶ እንዲያሰማ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው (ቁ.121) ::
- ከዚህ በተጨማሪ ተከሳሹ ቃሉን መስጠት የፈቀደ (የፈለገ) እንደሆነ በመጀመሪያ ቃሉን መስጠት አለበት:: ሆኖም በሚሰጠው ቃል ላይ መስቀለያ ጥያቄ ሊጠየቅ

እንደማይችልና ነገር ግን ፍ/ቤቱ ነገሩን ለማብራራት መጠየቅ እንደሚችል ሕጉ አስቀምጧል (ቁ.143(3)):: ይሁን እንጂ ተከሳሹ የሚሰጠው ቃል የተመሰከረበትን ነገር ከመከላከል አንፃር ምን ፋይዳ እንዳለው ሕጉ በግልፅ ያለው ነገር የለም ብቻ ሳይሆን በማስረጃነት ሊጠቅም የሚችል ቢሆን ኖሮ ለምን መስቀልያ ጥያቄ እንዳይጠየቅ ተከለከለ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው:: የመከላከያ ማስረጃነት ደረጃ (status) አይኖሮውም ማለት ግን ምንም ጠቀሜታ የለውም ሊባል ኣይችልም:: በማስረጃ ምዘና ጊዜ ግምት ውስጥ ሊገባ የሚችል ነጥብ የያዘ ሊሆን ስለሚችልም ፋይዳው ከዚህ ኣንፃር ቢታይ ጥሩ ነው የሚል እምነት ኣለኝ:: ሕጉም ያለምንም ጥቅም ያካትታል ተብሎ መቼም ቢሆን አይታሰብምና ነው::

- የተከሳሹን መከላከያ ምስክሮች አጠያየቅ፣ የጥያቄዎቹን ዓይነትና የምስክርነት ቃል አመዘጋገብን በተመለከተ ከላይ ስለ ዓ/ሕግ ምስክሮች የተገለፀው ተፈፃሚ ስለሆነ ደግሞ መፃፍ ድግግሞሽ የሚፈጥርና አስፈላጊነት የሌለው በመሆኑ በዚሁ ታልፏል::

2.7.5 በማስረጃ ረገድ የፍርድ ቤት ሚና

- በማስረጃ ረገድ ፍርድ ቤቶች (ዳኞች) ያላቸው ሚና ስንመለከት በዓለማችን በሚገኙ ሁለት ዋና ዋና የሕግ ስርዓቶች ልዩነት ይታያል::
- **በኮመን ሎ የሕግ ስርዓት** (Common Law Legal System) **በሚከተሉ አገሮች የክርክሩ አድማስና ስትራቴጂ የሚወስኑት፤** ማስረጃን የማቅረብና የመጠየቅ በዋነኝነት ሰፊ ሚና ያላቸው ተከራካሪ ወገኖች ናቸው፤ በዚህ ረገድ የዳኛው ሚና በጣም ውሱን ነው::

  ለምሳሌ፡_ምስክሮችን መጠየቅ የሚችለው ግልፅ ያልሆነ ነገር እንዲብራራ ለማድረግ ነው::አልፎ በጣም ኣስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል:: አጠራጣሪ ሆኖ ያገኘውን የእምነት ቃል ውድቅ ለማድረግ ይችላል::
- **በሲቪል ሎ (ኮንቲኔንታል)** የሕግ ስርዓት ያለው አሰራር ስናይ ግን የክርክሩ ስትራቴጂ የሚቀይሰው፣ የክርክሩ ኣድማስ የሚወስነው፣ የትኛው ማስረጃ መቅረብ እንደለበትና እነደሌለበት ከመወሰን ኣኳያ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት፣ በዋነኝነት ለምስክሮች ጥያቄ የሚያቀርብ፣ ወዘተ ዳኛ ነው::
- በእኛ አገር የሕግ ስርዓት በመሰረቱ ማስረጃ ማቅረብና ምስክሮችን መመርመር የዓ/ሕጉና የተከሳሹ ሃላፊነት ቢሆንም **ፍ/ቤቱም ውስን ሚናዎች እንዳሉት ማየት**

ይቻላል::ፍ/ቤቱ በምስክር አቀራረብና ምርመራ ያለውን ሚና ሲጫወት ገለልተኛነቱን (Impartiality) በማይነካና በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚገባ መርሳት የለብንም:: ስለዚህ ይህንን እንደመነሻ በመያዝ የፍ/ቤቱ ሚናዎች ምን እንደሆኑ እናያለን፡-

- ሀ) **ምስክሮችን መመርመር** (መጠየቅ) በዋነኛነት የባለጉዳዮች ሃላፊነት ቢሆንም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍ/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ምስክሮቹን **ማናቸውንም ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል** (ቁ.136 (4))። **ይህም በተለምዶም የፍርድ ቤት ማጣሪያ ጥያቄ እየተባለ ይጠራል**:: ከሕጉ አነጋገር ተነስተን ዳኞች ምን ዓይነት ጥያቄ ማንሳት አለባቸው ብለን እናስብ ይሆናል፡፡ሕጉ የሚለው **“ማናቸውንም”** ጥያቄ ነው:: በተግባር ያለው አካሄድ በተለይ ያለ ጠበቃ የሚከራከሩ ተከሳሾች የዋና ጥያቄ ምንነትና እንዴት እንደሚቀርብ ባለማወቃቸው ወደ ማዘበራረቅ ስለሚገቡ ዳኞች ራሳቸው ዋናው ጥያቄ ሳይቀር ሲጠይቁላቸው ይታያል::

- ከዚህ በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች የምስክሮች አመሰካከር መቆጣጠር ይገባቸዋል፡፡ **አሳድር እና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለው ማስረጃ ብቻ** ትኩረት እንዲያደርጉ መቆጣጣር ያስፈልጋል፡፡፡

- **ለ)ዳኞች ተጨማሪ ምስክር እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላሉ**:: በዚህም መሰረት፤ (1) **ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ** ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም ምስክር መጥራት ይችላል (ቁ.143 (1))::ማንኛውንም ምስክር ሲል ስለጉዳዩ እውቀት አለው ተብሎ በፍ/ቤቱ ግምት የተወሰደበት ሰው ነው፡፡(2) **ዓ/ሕጉና ተከሳሽ በምስክር ዝርዝር ላይ ያልተጠቀሱ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው በጠየቁ ጊዜ ምስክሮቹ ነገሩን ለማዘግየት ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትሕ ኣስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሮቹ እንዲጠሩ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.143 (2))** :((3) **ተከሳሽ ለቀረበበት ክስ የእምነት ቃል የሰጠ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ኣስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዓ/ሕጉ ለክሱ የሚደግፈውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ለማዘዝና ተከሳሽም መከላከያውን እንዲያቀርብ ለመፍቀድ እንደሚችል ነው** (ቁ.134 /2/ ይመለከቷል)::

- በወ/ህ/ቁ. 134(2) እና በቁ.143(1) እና (2) ከተመለከተው ውጭ ዳኛው የቀረበለትን ጉዳይ በተመለከተ ማስረጃ ለመፈለግ የግሉን ምርመራና ምርምር (Investigation and research) ማድረግ የለበትም::
- ስለዚህ ማስረጃን በማቅረብና በመመርመር ረገድ የዳኛ ሚና ሲታይ የተያዘው ጉዳይ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲያገኝ ወይም የተሳሳተ ውሳኔ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የኮንቲኔንታል የሕግ ስርዓት እንደሚያደርጉት ባይሆንም በእኛ አገርም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው::በተለይ ዝቅተኛ የሕግ እውቀትና ያነሰ የመከራከር ችሎታ ባለበት እና በጠበቃ እንዳይከራከር ዓቅም በሌለው ሕ/ሰብ ውስጥ ዳኞች የጎላ ሚና ይኖራቸዋል::

2.7.6 የመዝጊያ ንግግር

- የመዝጊያ ወይም የክርክሩ ማቆሚያ ንግግር የሁለቱም ተከራካሪዎች ወገን ምስክሮች ተሰምተው ካለቁ በኃላ፣ ተጨማሪ ምስክሮች ቀርበው ከሆነም ከተሰሙና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችም ካሉ ተጠቃልለው ከቀረቡ በኃላ ዓ/ሕጉና ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የሚያቀርቡት ነው:: የመዝጊያ ሓሳቡ የሚቀርበውም በቃል እንጂ በፅሑፍ እንዳልሆነ ከሕጉ የቋንቋ አጠቃቀም (ይናገራል ስለሚል) መረዳት ይቻላል:: ሆኖም ሲሰራበት የነበረና አሁንም ሙሉ በሙሉ ቀርቷል ለማለት የማያስደፍረው ተከራካሪዎች የመፋረጃ ሓሳባቸውን ወይም የመዝጊያ ንግግራቸውን ለማቅረብ ቀጠሮ እነዲሰጣቸው ሲጠየቁ ፍ/ቤትም እንደሚፈቅድላቸው ነው:: የመፋረጃ ሓሳብ እየተባለ ሲቀርብ የነበረውም በቃል ሳይሆን ብዙ ሓተታ ያለበት በፅሑፍ ነበር::
- የመዝጊያ ንግግሩን መጀመሪያ የሚያቀርበው ዓ/ሕጉ ሆኖ፤ ንግግሩ መሰረት የሚያደርገው ደግሞ በክሱ ማመልከቻ ላይ በጠቀሰው የሕግ ዓንቀፅ መሰረት ወይም በሌላ ያስረዳ መሆኑ ኣለመሆኑን፣ ተከሳሽ ጥፋተኛ መደረግ ያለበት መሆኑ ኣለመሆኑን ነው።። ተከሳሹ ተመስክሮበታል የሚል እምነት ካለው ጥፋተኛ እንዲባልለት: በመከላከያ ማስረጃው ኣፍርሶታል (አስተባብሎታል) የሚል እምነት ከያዘ ደግሞ በነፃ ይለቀቅ የሚል ኣስተያየት ሊሰጥ ይገባል (ቁ.148 (1))::
- ዓ/ሕግ ንግግሩን ካቆመ በኋላ ቀጥሎም ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ስለ ሕጉና ስለማስረጃው ሁኔታ ይናገራል:: የዐ/ሕግ ማስረጃን በመከላከያው ያፈረሰው መሆኑን በነፃ ሊለቀቅ እንደሚገባ ወይም ወደ ቀላል ዓንቀፅ መለወጥ የሚገባው መሆኑ

አለመሆኑን ወዘተ ይገልፃል:: ተከሳሾቹ ብዙ ከሆኑ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ንግግር የሚያደርግበትን ተራ ፍ/ቤቱ ይወስናል::

- የመዝጊያ ንግግር ማድረግ ግዴታ ባለመሆኑ ሁለቱ ተከራካሪዎች ወገን ከፈለጉ የሚያደርጉት ነው:: ንግግር እንደሚያደርጉ ተጠይቀው ፈቃደኞች ካልሆኑ ካላቀረባችሁ ብሎ ፍ/ቤቱ የሚያስገድድበት ሁኔታ መኖር የለበትም::

III- ስለ ፍርድና ቅጣት

ስለ ፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ

- ፍርድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ **የወ/መ/ሕ/ስ/ስ ያስቀመጠው ትርጉም ባይኖርም** ከስነ ስርዓቱ አጠቃላይ ይዘት አንፃር ሲታይ፣ ፍርድ ማለት በከሳሽ ወገን የተመሰረተ ክስ እና በሁለቱ ወገኖች የቀረበ ማስረጃ ይዘት አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሮ ተከሳሽን ነፃ ወይም ጥፋተኛ የሚያድግ ውሳኔ የያዘ የፅሁፍ ሃተታ ነው፡፡
- የፍርድ ዓላማ በዓ/ሕግ ወይም በግል ከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ሲካሄድ የቆየው ክርክር **በተቻለ መጠን ኣጭር፣ ግልፅ፣ በምክንያት ላይ የተመሰረተ፣ ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ** ለባለጉዳዮችና ለህዝቡ ለመግለፅ (ለመንገር) ነው:: ይህን ዓላማ ለማሳካት ዳኞች ፍርድ በሚፅፉበት ጊዜ የክስ (ፍሬ ነገር) ፣የማስረጃና የሕግ ስነ ምክንያታዊ ትስስር (logical interrelation) በሚያሳይና በምክንያት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት::
- ፍርድ የሚሰጠው ዓ/ሕጉና ተከሳሹ ወይም ጠበቃው የመዝጊያ ሓሳባቸውን ካሰሙ በኃላ መሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.149 (1) ስር ተመልክቷል፡፡
- ክሱ ከአንድ በላይ በሆኑ ዳኞች የሚታይ ከሆነ ዳኞቹ በሕግ ጉዳይና በማስረጃው ላይ ሞያዊ ውይይት ያደርጋሉ::በዚህ መሰረት ውሳኔ ማግኘት ያለባቸው **ነጥቦች (ጭብጦች) ለይተው ያወጣሉ።**
- ፍርዱም **በሙሉ ድምፅ ወይም በድምፅ ብልጫ** ሊሰጥ ይችላል:: በድምፅ ብልጫ የተወሰነ እንደሆነ በሓሳብ የተለየው ዳኛ የተለየበትን ምክንያት **በመግለፅ የራሱን ሓሳብ በፅሑፍ ማስፈር አለበት** ። በድምፅ የተለየው ዳኛ ሓሳቡን በፅሑፍ ሲያስቀምጥ በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ የሰጡትን **ዳኞች መዝለፍና ማንቋሸሽ የለበትም።** ከእነሱ የተለየበትን የፍሬ ነገር አስተያየት ወይም የሕግ አተረጓጎም ብቻ ነው ማስቀመጥ ያለበት።

- የሚሰጠው ፍርድ የቀረበውን ክስና በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ቀርቦ የተሰማው ማስረጃ አጭር መግለጫ (Summary) ፍ/ቤቱ ማስረጃውን የተቀበለበትን ወይም ያልተቀበለበትን ምክንያቶች፣ ፍርዱ የተመሰረተበትን ሕግ መጥቀስና ጥፋተኛም ሆኖ በተገኘ ጊዜ ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ ዓንቀፅ መጥቀስ አለበት። ፍርዱም ቀን ተፅፎበት ፍርዱ በሰጠው ዳኛ ወይም ዳኞች መፈረም አለበት (ቁ.149 (1)) ።
- **የፍርድ አፃፃፍ የራሱ የሆነ የአፃፃፍ ጥበብ (art) ያለበት፣ ከሌሎች ፅሑፎች የሚለይበትም የሕግ ባለሙያ ስለሚፅፈው ብቻ ሳይሆን ገላጭ በሆነ ቋንቋ የሚፃፍ፣ የህሊና ፍርድና ሰብኣዊ አረዳድ የሚጠይቅ ልዩ ባህሪ ያለው፣ ከዚህ የተነሳም በሰዎች ላይ ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል ነው። ስለዚህ ከሌላው ተራ ስነጽሁፍ የተለየ እና ልዩ ጥንቃቄ የሚሻ ነው።።**
- በአጭሩ በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥና የሚፃፍ ፍርድ ሶስት መብቶችን ማለትም በአጠቃለይ የሕ/ሰቡ፣ በተለይ ደግሞ የተከሳሹና የወንጀሉ ሰለባ የሆኑትን ሰዎች መብት የሚነካ በመሆኑ ዳኞች በእነዚህ ባለመብቶች በተለይ ደግሞ በተከሳሹና በተበዳዩ እግር ቆሞው ነገሮችን በጥልቀትና አስተዋይነት በተሞላበት መዝገቡን በመመርመር የማያወላዳ ፍርድ ሊሰጡና ሊፅፉ ይገባል።
- የፍርድ አፃፃፍ በሌላ የስልጠና መርሃ ግብር የተሰጠ እና ወደ ፊትም የሚሰጥ በመሆኑ የዚህ ስልጠና አላማ አይደለም።።ይሁን እንጂ የፍርድ አፃፃፍ ከወንጀል ጉዳዮች ጋር አገናዝበን የተወሰነ ነጥብ ማንሳት ተገቢ ነው።።በዚህም መሰረት ከወንጀል የፍርድ አፃፃፍ በተገናኘ የሚታዩ ችግሮች፡-

- ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ በግልፅ አለመጥቀስ
- በችሎት ስራ ላይ የተመዘገበው የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል ቃል-በቃል በፍርድ ላይ መገልበጥ
- የተንዛዛ እና በጣም ረጅም የሆነ ፍርድ መፃፍ።።
- የልዩነት ሃሳብ አለመጻፍ የመሳሰሉት ናቸው።።

የቅጣት አወሳሰን ስነ ስርዓት

- ቅጣት ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘ ሰው የሚሰጥና ጥፋተኛ የተደረገበት ዓንቀፅ የሚያዝዘው የቅጣት ዓይነት መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው።
- ፍ/ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.149 (3-7) በመከተል ነው።
- የእነዚህ ንዑሳን ቁጥሮች ይዘትም፡- ተከሳሽ ጥፋተኛ ነው በተባለ ጊዜ ስለቅጣት ማክበድ ወይም ማቅለል ዓቃቤ ሕጉ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ

ይጠይቀዋል። ዓቃቤ ሕጉም ስለተከሳሹ ጠባይ (character) ለማስረዳት ምስክሮች ለመጥራት ይችላል። ዓቃቤ ሕጉ ስለቅጣቱ አስተያየቱን ከሰጠ በኃላ ተከሳሽ ወይም ጠበቃው መልስ የመስጠት መብት ኣለው፣ ስለጠባዩም ለማስረዳት ምስክሮች ለመጥራት ይችላል። ተከሳሹ ቀድሞ በጥፋተኝነት አልተፈረደብኝም ያለ እንደሆነ ዓቃቤ ሕጉ ከዚህ ቀደም በጥፋተኝነት የተፈረደበት ለመሆኑ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለበት የሚል ነው።.

- ከእነዚህ ንኡስ ቁጥሮች መገንዘብ እንደሚቻለው፤

1. ከጥፋተኝነት ውሳኔ በኃላ ዓ/ሕጉ ስለ ቅጣት ማክበድ ወይም ማቅለል አስተያየት ካለው እንዲገልፅ ፍ/ቤ እንደሚጠይቀውና ዓ/ሕጉም ስለተከሳሹ ጠባይ ለማስረዳት ምስክሮችን የመጥራት መብት አለው።
2. ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ስለ ቅጣቱ መልስ ይሰጣል። መልስ መስጠት ብቻ ሳይሆን ስለቅጣት ማቅለያ ሓሳብ ሊያቀርብ ይችላል።
3. ዓ/ሕግ ተከሳሹ የወንጀል ሪከርድ እንዳለው አስረድቶ ተከሳሹ ግን ይህ ሁኔታ ከካደ ዓ/ሕጉ ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳት አለበት።
4. የቅጣት ክርክሩ ከተጠናቀቀና ካስፈለገም ስለቅጣቱ ማስረጃ ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ይወስናል። ቅጣቱ የተሰጠበትን የሕግ ቁጥርም መግለፅ አለበት።
5. በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ባለው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት የወንጀሉ ደረጃ በማውጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ከተመዘገቡ በኋላ በመጨረሻ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሳኔ ይሰጣል።

ማጠቃለያ

- በሕገመንግስታችን እና በወ/መ/ስ/ስ/ሕጋችን መሰረታዊ የሚባሉ የክስ አሰማም ሂደት የሚወስኑ፣የተከራካሪ መብትና ግዴታ የሚገልፁ ድንጋጌዎች ተካትተው ይገኛሉ።
- ይሁን እንጂ የስነ ስርዓት ሕጉ በርከት ያሉ ክፍተቶች ያሉበት ቢሆንም ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ተከትሎ ያለመስራት ችግር እንዳለም ግልፅ ነው።
- በሕጉ መሰረት አለመስራት ደግሞ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሲያስከትል የቆየና አሁንም እያስከተለ ያለ ነው።
- እነዚህ ድንጋጌዎች አንድ የወንጀል ክስ ለመስማት ተከሳሹ በአካል መቅረበ እነዳለበት ብቻ ሳይን አስቀደሞ ለመከላለል የሚያስችለው ዝግጅት እንዲያደርግ የክሱ ግልባጭ ቀደም ብሎ ሊደርሰው እንደሚገባ፣ ክሱ በግልፅ ችሎትና በአፋጣኝ መሰማት

እንዳለበት አበክረው ያስገነዝቡናል፡፡በእነዚህ ግልፅ ድንጋጌዎች መመራት ንፁሃን ሰዎች ባልሰሩት ወንጀል እንዳይጎዱና ወንጀለኞችም በአፋጣኝ ጥፋታቸውን ተረጋግጦ የሚገባቸውን ቅጣት እንዲያገኙ ይረዳል፡፡

- ስለሆነም ተጎጂዎች ወንጀል በመፈፀም ጉዳት ያደረሱባቸውን ሰዎች ሲቀጡላቸው እርካታ ይሰማቸዋል፣ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ ለመጠየቅም አስተማማኝ ማስረጃ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፣ ሕ/ሰቡ በአጠቃላይ ደግሞ ወንጀል የፈፀሙትን ሰዎች ሲቀጡለት በፍትሕ ስርዓቱ ከፍተኛ አመኔታ ያሳድራል፡፡ በተለይዩ የልማት ስራዎች በልበ ሙሉነት ተሳታፊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡
- በአጠቃላይ የወንጀል ፍትሕ ስርዓቱ **ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊ፣ ተገማችና ውጤታማ** እንዲሆን ለማድረግ ሃላፊነት ተሰምቶአቸው በሃቀኝነት፣ በብቃትና ሕግን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች /በተለይ ዳኞችና ዓቃቤነ ሕግ/ ያሰፈልጋሉ፡፡